

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

" ሸምጋይ ቴአትር " ከተውኔት አላባውያን አንፃር ትንተና

በ

ሔርሜላ ምልክት

በማህበረሰብ ሳይንስና ስነ ሰብ ኮሌጅ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለባችለር ኦፍ አርትስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

ግንቦት 2017ዓ.ም

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

" ሸምጋይ ቴአትር " ከተውኔት አላባውያን አንፃር ትንተና

በ

ሔርሜላ ምልክት

የጥናቱ አማካሪ

መምህርት ጫልቱ ተሰማ

በማህበረሰብ ሳይንስና ስነ ሰብ ኮሌጅ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለባችለር ኦፍ አርትስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

ግንቦት 2017ዓ.ም

የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪው ስም_____

ፊርማ_____

ቀን_____

ይህ ጥናት በሄርሜላ ምልክት ቴአትር ከተውኔት አላባዊያን አንፃር በሚል ርዕስ የሰራችውን የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ፅሁፍ የዩኒቨርስቲውን ጥራት እና ደረጃ ያሟላ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት መሆኑን ማረጋገጫ ነው።

ይህም በፈታኝ ኮሚቴ ተረጋግጧል።

ፈታኝ አንድ

ስም_____

ፊርማ_____

ቀን_____

ፈታኝ ሁለት

ስም_____

ፊርማ_____

ቀን_____

ምስጋና

ከሁሉም አስቀድሜ መቸር፣ መስጠት ለማይታክተው ለዓለም ንጉስ ለሆነው ልዑል እግዚአብሔር እና ለእናቱ ቅድስት ድንግል ማሪያም ምስጋና ይድረሳቸው ። ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ በምሰራበት ወቅት በትዕግስት እና በትጋት በፍፁም ትህትና ስህተቴን በማረም በማስተካከል ጠቃሚ ሀሳብ በመስጠት ከፍተኛ ድጋፍ ላደረገችልኝ አማካሪዬ መምህርት ጫልቱ **ተሰማ** ምስጋናዬ እጅግ ከፍ ያለ ነው ። ከዚህ በመቀጠል በቃለ መጠይቁ ወቅት እና ተውኔቱን እንዳገኝ ቀና ትብብራቸውን ላደረጉልኝ የሸምጋይ ቴአትር አዘጋጋጆች ምስጋናዬ እጅግ ከፍ ያለ ነው። በመጨረሻም ከፈጣሪ በታች ሙሉ ህይወታቸውን ገብረው እዚህ እንድደርስ ብዙ ዋጋ ለከፈሉልኝ በቃላት ለማልገልፃቸው ለአባቴ ምልክት ሙልጌታ እና ለውድ ለእናቴ እንዲሁም የራሷን ህይወት ሳትኖር ለኔ ለኖረችው ውድ እህቴ ዳግማዊት ምልክት በተጨማሪም ለአክስቶቼ እና ለአጎቶቼ ከምስጋና በቀር የምከፍላቼሁ ስለሌለኝ ፈጣሪ ዕድሜ እና ጤና ይስጣችሁ ።

አበርክቶ

እሷ ሳትኖር ለኔ ለኖረችው የእርሷን ህይወት ትታ እኔ ህልሜን እድኖር ለረዳችኝ ላገዘችኝ፤የእነሷን ፍላጎት ሳታሳካ ለኔ በመጨነቅና በማሰብ ላስተማረችኝ ውድ እናቴ እንዲሁም ለአባቴ ይሁንልኝ ።

አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ " ሸምጋይ " ቴአትር ከተውኔት አላባዊያን አንፃር በሚል ርዕስ የቀረበ ነው ። ይህንን ርዕስ መሠረት በማድረግ አጥኚዋ ዓይነታዊ የምርምር ዜዴ ተጠቅማ የጥናት ወረቀቷን አጠናክራለች። ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ውስጥ የተለያዩ የመረጃ መሠበሰቢያ ዘዴዎች ቢኖሩም አጥኚዋ በመረጃ መሠብሠቢያነት የተጠቀመችው በዋናነት ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ ናቸው። በመጠቀም " የሸምጋይ " ቴአትር የነበረውን የገፀ ባህሪያት አሳሳል እና አምስቱ የተውኔት አላባዊያን እንዴት እንደቀረቡ በመተንተን ገልፃለች ። ሸምጋይ ተውኔት ውስጥ ያሉት ገፀ ባህሪያ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል መንገዶች አጥኚዋ ቴአትሩ በመመልከት ምን እንደሚመስል ትንተና አድርጋለች።እንዲሁም በሸምጋይ ተውኔት ውስጥ ያሉ አንዳን ቃላቶች ለመረዳት አስቸጋሪ እና ኢ-መደበኛ የሆኑ ቃላቶችን አጥኚዋ ተውኔቱን በምታነብበት ወቅትም ሆነ ቴአትሩን ስትመለከት ማየት ችላለች ይህም አጥኚዋ ክፍተት ናቸው ብላ በምዕራፍ ሶስት ገልፀዋለች።

ማውጫ ገፅ
ምስጋና II
አበርክቶ III
አጠቃሎ IV
ምዕራፍ አንድ 1
1.መግቢያ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 2
1.3 የጥናቱ ዓላማ 2
1.3.1 የጥናቱ ዓብይ ዓላማ 2
1.3.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ 2
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ 3
1.5 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች 3
1.6 የጥናቱ ወሰን 3
1.7 የጥናቱ ዘዴ 3
1.7.1 የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ 4
1.7.1.1 ቃለ መጠይቅ 4
1.7.1.2 ምልከታ 4
1.8 የጥናቱ አደረጃጀት 4
1.9 በጥናት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች 4
ምዕራፍ ሁለት 6
2.የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት 6
2.1የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት 6
2.1.1 የቴአትር ምንነት 6
2.1.2 የተውኔት ምንነት 7

2.2 የተውኔት አላባዊያን 8
2.3 መቼት 9
2.3.1 አጠቃላይ መቼት 10
2.3.2 ውስን መቼት 11
2.4 ገፀ-ባህሪ 11
2.4.1 የገፀ-ባህሪያት አይነቶች 12
2.4.1.1 ዓብይ/ወጥ ገፀ-ባህሪ 12
2.4.1.2 ንዑስ ገፀ ባህሪያት 12
2.4.1.3 አቀንቃኝ ገፀ-ባህሪ 13
2.4.1.4 ፀረ-አቀንቃኝ ገፀ-ባህሪ 13
2.4.1.5 ሰናይ ገፀ-ባህሪ 13
2.4.1.6 እኩይ ገፀ-ባህሪ 13
2.4.1.7 አስተኔ ገፀ-ባህሪያት 13
2.4.2 የገፀባህሪ አሳሳል ደረጃዎች 14
2.4.2.1 አካላዊ የገፀባህሪ አሳሳል ደረጃ 14
2.4.2.2 ማህበራዊ የገፀባህሪ አሳሳል ደረጃ 14
2.4.2.3 ስነ ልቦናዊ የገፀባህሪ ኣሳሳል ደረጃ 15
2.4.2.4 ሞራላዊ የገፀባህሪ የአሳሳል ደረጃ 15
2.5 ሴራ 15
2.5.1 የሴራ አይነቶች 16
2.5.1.1 ጥብቅ ሴራ 16
2.5.1.2 ጥምር ሴራ 16
2.6 ቃለ ተውኔት 17

2.7 ጭብጥ 18

ምዕራፍ ሶስት 19

3. የመረጃ ትንተና 19

3.1 ጭምቅ ታሪክ 19

3.2 የተውኔት አላባውያ ትንተና 20

3.2.1 የሸምጋይ ተውኔት የመቼት ትንተና 20

3.2.2 የሸምጋይ ተውኔት አጠቃላይ የመቼት ትንተና 20

3.3 የገፀ-ባህሪያት ትንተና 21

3.3.1 የሸምጋይ ተውኔት ወጥ ገፀ-ባህሪያት 21

3.3.1.1 የአለቃ ገብረሃና አካላዊ አሳሳል ደረጃ 21

3.3.1.2 የአለቃ ገብረሃና ማህበራዊ አሳሳል ደረጃ 22

3.3.1.3 የአለቃ ገብረሃና ስነ ልቦናዊ አሳሳል ደረጃ 22

3.3.1.4 አለቃ ገብረሃና ሞራላዊ አሳሳል ደረጃ 23

3.3.1.5 የማዘንጊያሽ አካላዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል 24

3.3.1.6 የወ/ሮ ማዘንጊያሽ ማህበራዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል 24

3.3.1.7 የወ/ሮ መዘንጊያሽ ስነ ልቦናዊ አሳሳል 25

3.3.1.8 የወ/ሮ ማዘንጊያሽ ሞራላዊ አሳሳል 25

3.3.1.9 የተክሌ አካላዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል 26

3.3.1.10 የተክሌ ማህበራዊ አሳሳል 26

3.3.1.11 የተክሌ ስነ ልቦናዊ የገፀ ባህሪ አሳሳል 26

3.3.1.12 የተክሌ ሞራላዊ አሳሳል 27

3.3.1.13 የጌታነህ አካላዊ አሳሳል 27

3.3.1.14 የጌታነህ ማህበራዊ አሳሳል 28

3.3.1.15 የጌታህ ስነ ልቦናዊ አሳሳል 29

3.3.1.16 የጌታነህ ሞራላዊ አሳሳል 29
3.3.1.17 የቦጅሮንድ አሞኜ አካላዊ አሳሳል 29
3.3.1.18 ቦጅሮንድ አሞኜ ማህበራዊ አሳሳል 30
3.3.1.19 ቦጅሮንድ አሞኜ ስነ ልቦናዊ አሳሳል 31
3.3.1.20 ቦጅሮንድ አሞኜ ሞራላዊ አሳሳል 31
3.3.1.21 የወታደር አካላዊ አሳሳል 32
3.3.1.22 የወታደር ማህበራዊ አሳሳል 32
3.3.1.24 የወታደር ሞራላዊ አሳሳል 33
3.4 የሴራ 34
3.5 ቃለ ተውኔት 35
3.6 ጭብጥ 35
ምዕራፍ አራት 36
4. ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳብ 36
4.1 ማጠቃለያ 36
4.2 የመፍትሔ ሃሳብ 36
ጥቅሶች ከመገኛ ቋንቋቸው 37
ዋቢ መፅሀፍት IX
አባሪ X
አባሪ 1 XI

ምዕራፍ አንድ

1.መግቢያ

ተውኔት የሰውን ልጅች አኗኗር፣ዕውቀት፣ልምምድ፣ሥራ፣ማህበራዊ እውነታ መርጦ ከማቅረቡ ባሻገር ወቅትን ፣ መኖርንና ሞትን፣ወንጀልንና ቅጣትን፣ጦርነትን፣ሠላምን፣ጀግንነት፣የበላይነትን በእውኑ አለም የሚከወኑ ሁነቶችንና በአለም ያለውን በመምረጥ የቴአትርን አላባውያንን እንዲያሟላ ተደርጎ፣ከቴያትር ዘውግ፣ስልት ተመርጦለት የራሱ በሆነ ቦታ ሕይወትን በመተርጎም ለማህበረሰቡ እንደመስታውት እራሱን እያሳየ እያዝናና የሚያስተምር ጥበብ ነው።ይህንንም ለማጠናከር ዘሪሁን አስፋው "የስነ-ፅሁፍ መሰረታውያን" በሚለው መፅሐፉ ላይ እንዲህ ገልጿል፦ " ተውኔት በደራሲው በተመረጠ ጠባብ ቦታና የጊዜ ክፍፍል ሕይወትን በመድረክ ላይ ስለሚያቀርብ ከሌሎች የስነ-ፅሁፍ በተለየ ለስሜታቻን ቅርብ ነው።" (ዘሪሁን፣2009፡261) እንዲህ በማለት ሰለ ተውኔት ያብራራል።

ከላይ እንደምንረዳው ተውኔት በፀሀፈ ተውኔቱ ምናብ የተወለዱትን ገፀ ባህሪያት በተመረጠላቸው ቦታና ጊዜ የህይወታቸው ውጣ ውረድ በድርጊት በመድረክ የሚያሳይ የስነ-ፅሁፍ ዘርፍ ነው።ተውኔት ፀሀፈ ተውኔቱ በሚስላቸው ገፀ ባህሪያት የማህበረሰቡን ችግር እንደመስታውት ጉድፍን ነቅሶ እያሰየ በማስተማርና በማዝናና ረገድ ሚናው ከፍ የለ ነው። ይህንንም ለማጠናከር የስድስተኛ ክፍል የክወናና ዕይታ ጥበባት የተማሪ መፅሀፍ ላይ " ተውኔት የሰው ልጆችን የእለት ተእለት ገጠመኝ አስመስሎ እየቀዳ በጊዜ እና በቦታ ተወስኖ የሚከወን ታሪክ ነው።" (2014: የ6ኛ ክፍል የክወናናዕይታ ጥበባት መፅሀፍ) እንዲህ በማለት ሰለ ተውኔት ያብራራል። ይህ ፅንስ ሀሳብ ሲብራራ ተውኔት የስነ-ፅሁፍ ዘርፍ ሲሆን የሰው ልጆችን ሕይወት በመድረክ በሚመች መልኩ በፀሀፈ ተውኔቱ የምናብ ሰዎች አማካኝነት የሰዎችን ባህሪ አሳማኝ በሆነ መንገድ ስለሚያቀርብ ተደራስያንን ራሳቸውን እንዲመለከቱ ይበልጥ ይረዳቸዋል።ተውኔት የራሱ አካል ክፍሎች አሉት እነሱም፦ቃለ-ተውኔት፣ገፀ-ባህሪ፣ጭብጥ፣ሴራና መቸት ድምር ውጤት ነው።በለይም አጥኚዋ ሸምጋይ ቲየትር ከተውኔት አላባውያን አንፃር ስሰራ የተውኔቱን ታሪካዊ ዳር ምን እንደሚመስል ለመመልከት የሞከረች ሲሆን ይህ ቴአትር በውስጡ የተወሳሰበ እና የከረረ ሴራ ሲኖረው ከ1800 ዓ.ም በፊት የነበረውን የኢትዮጵያ ስርዓተ መንግስት የስልጣኔ ደረጃ በትቂቱም ቢሆን የሚዳስስ የተውኔት ታሪክ ያለው ነው። ኢትዮጵያ በቸለይ የጎጃም ፣ የጎንደር፣ የሸዋ እና የትግሬ መኳንንቶች በማለት ተከፋፍላ የምትመራ የነበረች ቢሆንም ኢትዮጰያን አንድ አድርጎ ለመግዛት የነበረውን የስልጣን ሽኩቻ በግልፅ የሚዳስስ የተውኔት ታሪክ ሲኖረው ዋናው ትኩረቱና መቼቱም በአለቃ ገብረ ሀና ቤት ውስጥ የተከናወነ ነው። ይህ ቴአትር የተውኔት አላባውያን የተባሉት በግልፅ የተቀመጡበትና እውነተኛ ታሪካዊ ዳራዎች የተዳሰሱበት ነው።በሆኑም አጥኝው በሀገራችን ኢትዮጵያ ከሚገኙት ቴአትር ቤቶች መካከል አንጋፋና እና ረጅም ዘመን ባስቆጠረው ብሔራዊ ቴአትር ቤት እየቀረበ ያለውን "ሸምጋይ ቴአትር"ከተውኔት አላባዊያን አንፃር ትንተና በሚል

ርዕስ ጥናቷን የሜታጠና ይሆናል።

1.1 የጥናቱ ዳራ

ተውኔት የሰው ልጆችን የዕለት ተዕለት የኑሮ ሂደትን የሚያሳይ ጥበብ ነው። ተውኔት የሰው ልጆች አኗኗር፣ አመለካከት እና የማህበራዊ ግንኙነት መሠረት በማድረግ የሚቀርብ የጥበብ ዘርፍ ነው። "ተውኔት የተጀመረው ግሪክ ሲሆን ግሪኮች የልምላሜ እና የወይን አምላካቸው ለሆነው ለዳይኖሰስ ምስጋና የሚያቀርቡበት ፌስቲቫል ላይ ህብረ ዘማሪያን ለዳይኖሰስ በሚያቀርቡበት ጊዜ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ነው የተጀመረው።"(የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት እና ምርምር ማዕከል ፣ 1993) ከላይ የተጠቀሰው ሀሳብ እንደሚያመለክተው ቴአትር የተጀመረው እና መደበኛ መልኩን የያዘው በግሪክ ሀገር እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ቴአትር የገሀዱ አለም ነጸብራቅ እንደመሆኑ የሰዉ ልጆችን ሀዘን ደስታ ፡ጥላቻና ፍቅርን ባጠቃላይ የእለት ተእለት እንቅስቃሴን በመድረክ ላይ ከነዉጣዉረዱ በገሀድ የሚያሳየን ድንቅ ስራ ነዉ።

ተዉኔት የትያትር ድርሰት ሲሆን ጸሀፊ ተዉኔቱ በድርሰቱ ዉስጥ ስም የተሰየመላቸዉን ገጸባህሪያት በመድረክ ላይ በተዋናይ አማካኝነት የገጸባህሪያቱን ሚና በመያዝ የሚያቀርቡበት ልዩ የመድረክ ስራ ነዉ።" የአንድ ተዉኔት መጀመሪያ የድርጊቱን ቦታ ፣ የድርጊቱን ወቅት ፣ የገጸባህሪን ማንነት፣ የተዉኔቱን ድባብ ምን ሊሆን (ሊፈጠር እንደሚችል) ይገልጻል ።" (የኢትዮጲያ ብሄራዊ ትያትር፣67፣2009) ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ቴአትር ማለት የሰውን ልጆች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴን ፤ ባህል ፤ የህይወት መንገድን ፤ ፖለቲካና ማህበራዊ ግንኙነቶችን ከሰው ልጆች በመውሰድ መልሶ ለሰው ልጆች የሚያቀርብ የጥበብ ዘርፍ ነው። ሸምጋይ ቴአትር ከዛሬ መቶ አመት በፊት በጎንደር አካባቢ ባሉ ሹማምቶችና ቀሳውስታት ላይ ያተኮረ ታሪክ ቢኖረውን በዋናነት ግን የሚያተኩረው በጎንደርና በሸዋው ሚኒልክ ላይ ያለ የስልጣን ሹኩቻ የሚያጠነጥን ነው። በተለይ የጎንደር አርበኞች የሚኒሊክ ኢትዮጵያን እንዳይገዛት ቡዙ ለማሸነፍ ከአለቃ ገብረ ሀና ዘንድ በመምጣት የጥበብ ምክር እንዲሰጧቸውና እንዴት ማሸነፍ እንደሚችሉ እንዲነግሯቸው አለቃ ገብረ ሀናን ቢጠይቋቸውም የሸዋውን ሚኒልክ አጥብቀው ይወዱ ስለነበር ምንም አይነት የጠሰበብ እውቀት አላካፍሏቸው ሲሉ ከነ አሸከሮቻቸው በማሰርና ቢያሰቃዩአቸውም ምንም አይነት ነገር ስላላገኙ በመጨረሻም የሸዋው ሚኒሊክ ይነግሳል።ተውኔት በሴራ ፣ በገፀ ባህሪ ፣ መቼት ፣ ሴራ እና ቃለ ተውኔት በማካተት ይፃፋል። ሸምጋይ ቴአትር ዋና ጭብጡ

ይህም ጥናት ሸምጋይ ቴአትር ከተውኔት አላባውያን ትንትና በሚል ርዕስ አጥኝዋ የምታጠና ይሆናል።

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚዋ "ሸምጋይ" የተሰኘውን ቴአትር ከተውኔት አላባዊያን አንፃር ጥናታዊ ጽሁፍ ለመስራት ያነሳሳት ዋነኛው ምክንያት ቴአትሩ መድረክ ላይ መታየት ከጀመረ አጭር ጊዜ ያስቆጠረ በመሆኑና ቴአትሩ ከተውኔት አላባዊያን አንፃር የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ አጥኝዋ ባለማየቷ ነው። እንዲሁም የቴአትሩን ከተውኔት አላባዊያን አንፃር መተንተን

በመፈለጓ ነው።

1.3 የጥናቱ ዓላማ

1.3.1 የጥናቱ ዓብይ ዓላማ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዓብይ ዓላማ "ሸምጋይ ቴአትርን" ከተውኔት አላባዊያን አንፃር መተንተን ነው።

1.3.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ

"ሸምጋይ " ቴአትር ውስጥ ያሉ ገፀ ባህሪያ አሳሳል በዝርዝር መመልከት።

"ሸምጋይ" ቴአትር የመቼቱ አገላለፅ በዝርዝር መመልከት።

." ሸምጋይ " ቴአትር የቃለ ተውኔት አጠቃቀሙ በዝርዝር ማየት።

" ሸምጋይ " ቴአትር ጭብጡ ምን ላይ ያተኮረ እንደሆነ ማየት።

"ሸምጋይ" ቴአትር የሴራ አወቃቀሩ በጥልቀት መመልከት።

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

"ሸምጋ" ቴአትር ከተውኔት አላባውያን አንፃር በመተንተን የተውኔት አላባውያንን በግልፅ የሚያስረዳ ይሆናል። በዚህ ጥናት ዙሪያ ጥናታዊ ፅሁፍ ለሚሰሩ አጥኚዎች ሆነ ሙያተኞች እንደ መረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላል።"ሸምጋይ" ቴአትርን ከተውኔት አላባዊያን አንፃር በግልፅ የሚያስረዳ ይሆናል። "ሸምጋይ" ቴአትር ከተውኔት አላባውያን አንፃር ማወቅ ለሚፈልጉ እንደ ግብዓት በመሆን የሚያገለግል ይሆናል።

1.5 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

"ሸምጋይ " ቴአትር ውስጥ ያሉ ገፀ ባህሪያ አሳሳል ምን ይመስላል?

"ሸምጋይ" ቴአትር የመቼቱ አገላለፅ ምን ይመስላል?

" ሸምጋይ " ቴአትር የቃለ ተውኔት አጠቃቀሙ ምን ይመስላል?

" ሸምጋይ " ቴአትር ጭብጡ ምንድን ነው?

"ሸምጋይ" ቴአትር የሴራ አወቃቀሩ ምን ይመስላል?

1.6 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ " ሸምጋይ " ቴአትር ከአምስቱ የተውኔት አላባዊያን ማለትም ገፀ ባህሪይ ፣ መቼት ፣ ቃለ ተውኔት ፣ ሴራ እና ጭብ አንፃር መተንተን ላይ ብቻ ይሆናል።

1.7 የጥናቱ ዘዴ

በአንድ ጥናታዊ ፅሁፍ ላይ ጥናታዊ ምርምር አካሂዶ የመፍትሔ ሀሳብ ለማቅረብ የሚረዱ መሠረታዊ የሆኑ የምርምር አይነቶች አሉ።ያለው እንዳወቅ መሠረታዊ የምርምር አይነቶችን እንዲህ በማለት ያብራራዋል። "*መጠናዊ ምርምር ከሰያሜው እንደምንረዳው መጠንን ገላጭ፣የመረጃ አይነትን በቁጥር የሚገልፅ እና መረጃዎችን በእስታቲክሳዊ ዘዴ የሚተነትን ሲሆን አይነታዊ ምርምር በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በማተኮር በቃለ መጠይቅ፣በምልከታ እና የመረጃ ትንተናን ዘዴ የሚያካትት የምርምር አይነት ነው።"(ያለው እንዳወቅ ፣ 20፣2006)* ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ ተጨባጭና ምክንያታዊ እንዲሆን ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ከጥናቱ ርዕስ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሰዎች፣ መፅሀፎች እና ጥናታዊ ፅሁፎች በመጠየቅ እና በማንበብ እንደ አስፈላጊነቱ ማጣቀስ የአጥኚዋ ተቀዳሚ ዘዴ ስለሆነ ጥናቱ ከአይነታዊ የምርምር ዘዴ ውስጥ ይመደባል። በመሆኑም አጥኚዋ አይነታዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅማ ሸምጋይ ቴአትር ሲቀርብ ቴአትሩን በመመልከት ፎቶዎችን በመያዝ ፣ ተውኔቱን በማንበብ እና በቴአትሩ ላይ የተሳተፉ ተዋንያኖችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ እንዲሁም ከጥናቱ ርዕስ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ፅሁፎች በመጠቀም መረጃዎችን የምትሰበስብ ይሆናል።

1.7.1 የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

አጥኚዋ ይሂን ጥናታዊ ፅሁፍ ለማዘጋጀት ይረዳት ዘንድ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን የምትጠቀም ሲሆን ይሄውም ቃለ መጠይቅ፣ምልከታ እና የመረጃ ትንተናን የምትከተል ይሆናል።

1.7.1.1 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ አለም እሸቱ "መሠረታዊ የምርምር እና የዘገባ አፃፃፍ" በሚለው መፅሀፍ እንዲህ በማለት ያብራራዋል።"ጠያቂው ከተጠያቂው ጋር በግንባር ተገናኝቶ በፅሁፍ ሳይሆን በቃለ ምልልስ የሚሰጣጡበት ሂደት ነው።"(አለም እሸቱ ፣ 65 ፣1995) ከዚህ እንደምረዳው አጥኚዋ ቃለ መጠይቅ በሚያደርግበት ጊዜ በአካል ተገናኝቶ አስፈላጊውን የድምፅ ቅጂዎችን በመጠቀም የሚደረግ የመረጃዎ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው።

1.7.1.2 ምልከታ

አለም እሸቱ "መሠረታዊ የምርምር እና የዘገባ አፃፃፍ" በሚለው መፅሀፍ ስለ ምልከታ እንዲህ በማለት ገልፆታል። "ምልከታ አይተን የምናልፈው ሳይሆን ለታቀደለት መሠረታዊ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ሲባል ሚከናወን ትኩረት እና ምርምርን የሚጋብዝ መረጃ መሰብሰቢያ ስልት ነው።"(አለም እሸቱ ፣ 69 ፣ 1995) ከዚህ እንደምንረዳው

ምልከታ ማለት ቴአትሩ በሚታይበት ቦታ እና ጊዜ በአካል በመገኘት ቴአትሩን ደጋግሞ በመመልከት፣በቪዲዮ በመቅረፅ እና በማስታወሻ በመፃፍ የሚቀርብ ጥናታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው። በመሆኑም አጥኚዋ ሸምጋይ ቴአትር በሚታይበት ወቅት ቴአትሩን በመመልከት ከተውኔት አላባዊያን አንፃር የምትዘረዝር ይሆናል።

1.8 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአራት ምዕራፎች እና በተለያዩ ንዑስ ክፍሎች የተደራጀ ነው። በምዕራፍ አንድ መግቢያ ፣ የጥናቱ ዳራ ፣ የጥናቱ አላማ ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ ፣ የጥናቱ ወሰን ፣የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣ የጥናቱ አደረጃጀት ፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሔ ሀሳብ ያጠቃልላል። በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት እና የንድፍ ሀሳብ ቅኝትን በሰፊው ለመዳሰስ ሞክራለች። በምዕራፍ ሶስት አራቱን የገፀ ባህሪያት አሳሳልእንዲሁም የተውኔት አላባዊያንን በሰፊ ለመቃኘት ሞክራለች። በምዕራፍ አራት ማጠቃለያ ፣ የመፍትሄ ሀሳብ፣ ጥቅሶች ከመገኛ ቋንቋቸው እና ዋቢ መፅሀፍትንና አባሪዎችን ይዟል።

1.9 በጥናት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

አጥኚዋ ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ በምትሰራበት ወቅት ያጋጠማትን ችግር አስቀምጣለች።

1. አጥኚዋ ተውኔቱን በምታነብበ ወቅት አስቸጋሪ የሆኑ ቃላቶችን በተውኔቱ ውስጥ ማግኘቷ እንዲሁም ቴአትሩን በምትመለከትበት ወቅት ተውኔቱ ላይ ያሉት ቃለ ተውኔቶች ቴአትሩ ላይ አለመኖር አጥኚዋን ጥናቷን በምትሰራበት ወቅት እነዚህ ችግሮች አጋጥመዋታን። ይህም ጥናቱ ውስንነት እንዲኖረው አድርጎታል።

ምዕራፍ ሁለት

2.የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት

አጥኚዋ ይሂንን ጥናታዊ ፅሁፍ ለመስራት ስትነሳ ከጥናታዊ ፅሁፏ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሃሳቦች በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ለመመልከት ሞክራለች። ነገር ግን አጥኚዋ ከቴአትር አላባዊያን አንፃር በሚል ርዕስ በቴአትር ላይ የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ ባለማግኘቷ " ተውኔት ትንተና ከተውኔት አለባውያን አንፃር " የሚለውን ተመልክታለች።ይህ ቴአትር ሀምሌ 2010 በአዲግራት ዩኒቨርስቲ በሔለን ልዑል ለቴአትር አርትስ ባችለር ድግሪ ማሟያ የተዘጋጀ ጥናታዊ ፅሁፍ ነው። ይህ ጥናት ደግሞ " ሸምጋይ " ታሪካዊ ቴአትር ከተውኔት አላባዊያን አንፃር የሚል ርዕስ ነው። ሁለቱን ጥናት አንድ የሚያደርጋቸው ሁለቱም ሰለ ተውኔት አላባዊያን የሚያብራሩ ሲሆን ልዩነታቸው ደግሞ አጥኚዋ " ሸምጋይ " ታሪካዊ ቴአትር በሚሰራበት ስዓት አምስቱን የተውኔት አላባዊያን እንዴት ተጠቅመውታል እንዲሁም ተዋናዮች ከተሰጣቸው ገፀ ባህሪያት አንፃር እንዴት ተስለዋን የሚሉትን የምተነትን ይሆናል።

2.1የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት

2.1.1 የቴአትር ምንነት

ስለ ቴአትር ታሪክ አመጣጥ የሻው ተሰማ " የተውኔት አፅናፍ መነፅር " በሚለው መፅሀፉ እንዲህ ቀማለት አብራርቶታል።

> *ተውኔት ወይም ቴአትር እንደሌሎች የኪነ ጥበብ ዘርፎች ማለትም እንደ ሙዚቃ ና ሰዕል በዚህ ጊዜ ተጀመረ ተብሎ የተቀመጠ ማሰረጃ ባይኖርም ከሙዚቃ ና ከሰዕል ያላነሰ እድሜ እንዳለው ይናገራል ። ሁኖም ግን ብዙ ሊቃውንት የሚስማሙበት ከክርስቶስ ልደት በፊት 2500 እስከ 3300 ዓ.ዓ ባሉት ዘመናት ሳይጀመር እንዳልቀረ ይናገራል ። ነገር ግን ከዚህ ጊዜ በፊት ምንም አይነት የቴአትር እንቅስቃሴ አልነበረም ማለት ሳይሆን መረጃ የተገኘባቸው ወቅቶች እነዚህ በመሆናቸው ነው። ሰለ ድራማ ወይም ቴአትር አጀማመር ሁለት የተለያዩ ሀሳቦች ይነሳሉ አንደኛው ለተውኔት መጀመር ከፍተኛ ሚና የተጫዎተችው ግብፅ ናት ስለዚህ ግብፅ ሀገር ተውኔት ተጀመረ ማለት እንችላለን የሚል ሲሆን ሁለተኛው ሀሳብ ደግሞ ለተውኔት መጀመር መሰፋፋት ግሪክን የሚስተካከላት የለም የሚሉት ናቸው ። ምንም እንኳ ሁለቱም ሀገራቶች የየራሳቸውን ምክንያቶች ቢያስቀምጡም የሰናዳ መረጃ በማስቅረብ ግሪክ ቀዳሚ ሀገር ሁና ተገኝታለች ። በመጀመሪያ ተቀርፆ የተገኘው ድራማ በግብፅ ሀገር ሲሆን " አባይደስ ፓሸን ፕሌይ " የተባለውን ድራማ እንደ ተመስገን እና አራጌ አገላለፅ የሚያጠነጥነው በግብፅ ሀገር ከሚገኙት አማልክቶች መካከል አንዱ የሆነው*

የኦስረስ አሟሟት ላይ እንደሚያተኩር ያስረዳል ። በግሪክ ቴአትር ወይም ድራማ አጀማመር መነሻ ነው ተብሎ ከሚታመነው አቴናውያን በየዓመቱ " ለዳይኖሲየስ " የተባለውን አምላካቸውን ለማመስገን ቀሚያደርጉት እንቅስቃሴ እና ሁነቶች እንደሆነ ይናገራል። (የሻው ተሰማ ፣ 1 ፣ 1998)

ከሀሳቡ እንደምንረዳው በዚህ ስነ -ስርዓት ላይ ይደረጉ የነበሩት እንቅስቃሴዎች ቀስ በቀስ ወደ ድራማ በማምጣት ድራማን (ቴአትር) ለመጀመር አስችሏቸዋል። በተጨማሪም ታላላቅ ፀሀፊያን የሚባሉት ኢርፒደስ ፣ ሶፈክለስ ፣ኤስክለስ ና አርስቶፋነስ በስራቸው አሁን ድረስ አድናቆትን የሚቸራቸው ታላላቅ ፀሀፊያንን ቀመፍጠር ትታወቃለች። ሮበርት ኮሔን" ቴአትር" በሚለው መፅሀፉ ስለቴአትር ታሪክ እንዲህ በማለት አብራርቶታል።

የቲያትር ታሪክ በጥንታዊ ሰልጣኔዎች የተመሰረተ ሲሆን እንደ ጥንታዊ ግሪክ ፣ ሮም ፣ ግብፅ እና ቻይና ባሉ ባህሎች ውስጥ የቲያትር ትርኢቶችን ያሳያል። በጥንቷ ግሪክ ቲያትር የሃይማኖታዊ በዓላት ዋነኛ አካል ነበር። ተውኔቶች ከቤት ውጭ ባሉ አምፊ ቲያትሮች ይደረጉ ነበር። እንደ ኤስክለስ ፣ሶፈክለስ እና ኢርፑደስ ያሉ የቴአትር ደራሲዎች ስራዎች አሁንም በቲያትር ላይ ላሳዩት ዘላቂ ተፅእኖ ይከበራሉ። በመካከለኛው ዘመን ቲያትር ወደ ሃይማኖታዊ ተውኔቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይካሄድ ነበር። በኋላም በተጓዥ ቡድኖች የሚከናወኑ ዓለማዊ ተውኔቶች ሆነዋል ። ህዳሴው በጥንታዊው የግሪክ እና የሮማውያን ቲያትር ላይ ፍላጎት እንዲያንሰራራ አድርጎታል ። ይሂም ቋሚ ቲያትሮች እንዲቋቋሙ እና የተዋናይ ኩባንያዎችን ወደ ሙያዊ ደረጃ እንዲያመራ በ17ኛው እና በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአውሮፓ ቲያትር ጉልህ እድገቶችን አጋጥሞታል። በዚህም እንደ ሞሊየር ፣ ሼክስፒር እና ኢብሰን ያሉ ተደማጭነት ያላቸው ፀሃፊዎች ብቅ አሉ። በ 19 ኛው ክፍለ ዘመን በቲያትር ውስጥ የእውነተኛነት መነሳት እንዲሁም እንደ ሜሎድራማ እና ሙዚቃዊ ቲያትር ያሉ አዳዲስ የቲያትር ቅርጾችን ታይቷል። በ 20 ኛው ክፍለ ዘመን ቲያትር የአቫንት ጋርደ እንቅስቃሴዎች ፣ የሙከራ ቲያትር እና እንደ በርቶልት ብሬክት ፣ አንቶኒን አርታውድ እና ኮንስታንቲን ስታኒስላቭስኪ ያሉ ደጋፊ ፀሀፊዎች እና ዳይሬክተሮች ተፅእኖ ስር ነቀል ለውጦች ታይተዋል። ይህ ወቅት ለቲያትር የዘመናዊ እና የድህረ ዘመናዊ አቀራረቦች እድገት እንዲሁም አዳዲስ የአፈፃፀም ጥበብ እና የመልቲሚዲያ ቲያትር እድገት ታይቷል። ዛሬ ቲያትር አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እንዲሁም የተለያዩ የተረት አተረጓጎም ቴክኒኮችን እና አዳዲስ አሰራሮችን እና አፈፃፀሞችን በማካተት በዝግመተ ለውጥ ቀጥሏል። የዘመናችን ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ጉዳዮችን የሚያንፀባርቅ እና የሚሳተፍ ጠቃሚ የጥበብ ቅርፅ ሆኖ ይቆያል። (ሮበርት ኮሔር ፣ 2011 ፣ 21)

የቲያትር አመጣጥ በሺዎች ለሚቆጠሩ አመታት እና የተለያዩ ባህሎች ያለው ረጅም እና ውስብስብ ታሪክ ያለው

ነው። ቀደምት የቲያትር ዓይነቶችን እንደ ግሪኮች፣ ሮማውያን እና ግብፃውያን ከመሳሰሉት ጥንታዊ ሥልጣኔዎች የተገኙ ሲሆን ትርኢትን እንደ መዝናኛ ፣ ትምህርት እና ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ዝግጅቶችን ለማስታወስ ይጠቀሙበት ነበ

2.1.2 የተውኔት ምንነት

ተውኔት እንደ ሌሎች የስነ-ፅሁፍ ዘርፎች በሰዎች ህይወት ውስጥ የሚኖር እና የማህበረሰብን ሀሳብ ፣ትውፊት ፣ ወግ እና ባህልን በማሳደግ ከፈተኛ ሚና የሚጫዎት የስነ-ፅሁፍ ዘርፍ ነው። ፊንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፌ ዘዴ " በተሰኘው መፅሀፋ ሊይ ስለተውኔት እንዲህ በማለት ያስቀምጠዎል። ተውኔት የሰውን ልጆች የእለት ተዕለት ገጠመኝ አስመስሎ እየቀዳ በጊዜ እና በቦታ ተወስኖ የሚመደረክ ታሪክ ነው። ተውኔት (ድራማ) የሚለው ቃል የተገኘው "ድራን" ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉም "ማድረግ" ወይም "መከወን" ማለት ነው።" (ፋንታሁን እንግዳ ፣ 2005፣9) ተውኔት የራሱ የሆነ ባህርያት ያሉት አንድ የስነ-ፅሁፍ ዘርፍ ሲሆን የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ ገፅታዎችንና ሁነቶችን አሰመስሎ ያንፀባርቃል። ትክክለኛውን የማህበረሰብ ገፅታን በማሳየት ረገድ ከላሎች የስነ-ፅሁፍ ዘርፎች የሚጋራቸው ኪነጥበባዊ ባህርያት አሉት። ነገር ግን ተውኔትን ከሌሎች የኪነ ጥበብ ዘርፎች ልዩ የሚያደርገው በተዋንያን አማካኝነት በመዴረክ ላይ የሚከወን ታሪክ በመሆኑ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ስለ ተውኔት ምንነት ጌታቸው በለጠ " የተውኔት ጉባኤ " በተሰኘው መፅሀፉ ላይ ስለተውኔት እንዲህ በማለት ያስቀምጠዋል። " ተውኔት የሚለው ቃል የተገኘው " ተዋናይ " ከሚለው የግዕዝ ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም ተጫወተ የሚለው ነው። ጭውውት ደግሞ በእንቅስቃሴ መዝናናት ሊሆን እንደሚችል መዘንጋት አይገባም" በማለት ይገልፀዋን።(ጌታቸው በለጠ ፣ 2004 ፣287)

ከሀሳቡ መሠዳት እንደሚቻለው ተውኔት መድረክ ላይ ከመቅረቡ በፊት ገፀ ባህሪያ የተውኔቱት ታሪክ ባህሪያት ያሉት አንድ የስነ-ፅሁፍ ዘርፍ ሲሆን እንደ ሌሎች የስ-ፅሁፍ ዘርፎች የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ ገፅታዎች ያንፀባርቃል።

2.2 የተውኔት አላባዊያን

የተውኔት አላባዊያን ተውኔትን ተውኔት የሚያሰኙ የአንድ ተውኔት የጀርባ አጥንት በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው። የተውኔት አላባዊያን ማለት የተውኔት አካል ክፍሎች ናቸው። ፊንታሁን እንግዲ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በተሰኘው መፅሐፉ ላይ ስለ ተውኔት አላባውያን እንደሚከተለው አስቀምጧል።

> *የተውኔት አላባውያን ማለት የተውኔት አካል ክፍሎ ናቸው። አንድ ቤት ከመሰረት እስከ ጉልላት ለመሰራት ሰሚንቶ ፣ አሸዋ ፣ ድንጋይ ፣ ብረት ፣ እንጨት ፣ ቆርቆሮ ፣ ምስማርና ቀለም ያስፈልገዋል።እነዚህ ቤትን*

ለመገንባት በዋናነት የሚያስፈልጉ አላባዎች ናቸው። በሌላ በኩል የሰው ልጅ ፍጡርየተገነባው ከሰጋ፣ከደም፣ ከአጥንት እና ከጅማት ነው። ወይም ከጥንታውያን ፈላስፎች እምነት የሰው ልጅ የተሰራው ከአፈር ፣ ከእሳትና ከነፋስ ነው። እነዚህም የሰው ልጅ የተሰራባቸው አላባዎች ናቸው።እንደነዚህም ሁሉ ተውኔት ሲፃፍ ግዴግዲ ፣ ማገርና ምሰሶ በመሆን የሚያገለግሉ ነገሮች በሞላ የተውኔት አሊባውያን በመባል ይታወቃሉ። (ፊንታሁን እንግዲ ፣ 2005 ፣10)

የተውኔት አላባዊያን ማለት አንድን ተውኔት ሙለ እንዲሆን የሚያደርጉ መሰረታዊ እና አስፈላጊ ነገሮች እንደሆኑ እንገነዘባለን፡፡ ተውኔት በሚፃፍበት ጊዜ ተውኔትን ተውኔት ሊያደርጉ የሚችሉ እንደ ግድግዳና ማገር እንዲሁም ምሰሶ በመሆን የሚያገለግሉ ለተውኔት የጀርባ አጥንት በመሆን የሚያገለግሉ የተውኔት አላባውያን ናቸው፡፡ የተውኔት አላባውያን በአንድ ተውኔት ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸው አምስቱ የተውኔት የአካል ክፍሎች ተብለው ይጠራሉ፡፡ አንድ ተውኔት ወደ መድረክ ከመምጣቱ በፊት ሊኖሩት የሚገቡ መሰረታዊና አስፈላጊ ነጥቦችን ያካትታል። ይህ ተውኔት ወደ መድረክ ሲመጣ ሂዎት በዘርቶ የተመልካቹን ስሜት ሰብስቦ እንዲይዝ የሚያስችል ሆኖ ታሪኩን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው መቆም እንዲችል መሰረታዊ የሆኑ የተውኔት አላባዊያንን ማካተት አለበት።

2.3 መቼት

መቼት የሚባለው የተውኔት አላባ በተውኔት ውስጥ ያለው ሚና ገፀባህሪያት የሚኖሩበትን ዘመንና ድርጊቱ የሚካሄድበትን ቦታ የሚጠቁም እንዲሁም ማህበራዊ እውነታዎችን የሚያሳይ ነው፡፡ መቼት የሚለው ቃል የመጣው ‹‹መቼ›› እና ‹‹የት›› ከሚሉት ቃላት ነው፡፡

በአጠቃላይ መቼት ሲባል ከጊዜ፣ ወቅቱና ቦታ ባለፈ የተውኔቱ ገፀባህሪያት የተቀረፁበት ዘመን የማህበረሰቡ ታሪካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ገፅታዎችን፣ማህበራዊ ግንኝነቶችን፣ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ክስተቶችን ወዘተ ሁሉ ያጠቃልላል (የስነ ድራማ መግቢያ፣2003፣ 22)

መቼት ተውኔቱ የሚካሄድበትን ቦታና ጊዜ ከማሳየት አልፎ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን መስተጋብሮች እውናዊ ሁኔታ የሚያሳይ ነው፡፡ በተውኔት ውስጥ ያሉትን ገፀባህሪያት ለማወቅ ከሚረዱ አላባዎች ውስጥ አንዱ መቼት ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ ገፀባህሪ ከሚኖርበት ቦታና የሚኖርበትን ጊዜ በማየት ያደገበትን ወይም እየኖረ ያለበትን ስፍራና እየኖረበት ያለውን ጊዜና ወቅት በማየት በየትኛው ዘመንና ወቅት ድርጊቱ እየተፈፀመ እንዳለ እንረዳለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የስድስተኛ ክፍል የክወናና ዕይታ ጥበብ መፅሀፍ ውስጥ ስለ መቼት እንዲህ ሲል

አስቀምጧል።

> *መቼት = መቼ፣ የት እና ማህበራዊ እውነታ የሚሉትን የሚያጠቃልል ሲሆን ተፈጥሯዊ ተውኔታዊ እንዲሁም አጠቃላይ እና ውሱን ተብለው ከሚያጠቃልሉት ጊዜ እና ቦታ አንጻር ይከፋፈላሉ። ከዚህ በተጨማሪም ከቦታ አንጻር የቤት ውስጥ፤ ከቤት ውጪ፤ ልዩ ልዩ እና ባዶ መቼት በመባል ይታወቃሉ። (የሰድስተኛ ክፍል የክወናና ዕይታ ጥበብ መፅሀፍ ፣ 2014 ፣ 12)*

መቼት በአንድ ተውኔት ውስጥ የተገለፁትን ቦታናየጊዜ እንዲሁም ማህበራዊ እውነታዎችን የማሳየት ከፍተኛ ሚና አለው። ተውኔት ከሰው ልጆች እውነተኛ እንቅስቃሴ የሚከተብ በመሆኑ ደራሲው ገፀባህሪያቱን ሊያስቀምጥ የሚችልበት ስፍራና ቦታ እንዲሁም ጊዜ መኖሩ የግድ ነው። ዘሪሁን አስፋው እህንን ሀሳብ ሲያጠናክረው እንዲህ ይላል።

> *የልብወለድ ገፀባህሪያት እንደ እውኑ አለም ሰዎች የመኖርያ አካባቢ ሊኖራቸው ይገባልና በልበወለድ አለማቸው የሚንቀሳቀሱትና ታሪካቸውን የሚፈፅሙበት ደራሲው በመረጠው የተወሰነ አካባቢ ሲሆን የሚኖሩበትና ታሪካቸውን የሚፈፅሙበት ጊዜ ፣ ወቅት፣ ዕለት እና ሰአትም ይኖራቸዋል። ይህ የገፀባህሪያቱ መገኛ ስፍራና ጊዜ በአንድ ላይ መቼት ይባላል።(ዘሪሁን አስፋው፣ 1996፣36)*

በተውኔት ውስጥ ያሉት ገፀባህሪያት ልክ በገሀዱ ዓለም እንዳለው ሰው የመኖሪያ ስፍራና ጊዜ ሊኖራቸው እንደሚገባ ነው።ይህም መቼት ከጊዜና ከቦታ አንፃር በዋናነት በሁለት ይከፈላል እነሱም፡- አጠቃላይ መቼት እና ውስን መቼት በመባል ይታወቃሉ።

መቼት የተውኔት አላባውያን ብለን ከምንዘረዝራቸው አንዱ እና ዋነኛው ነው ። መቼት ማለት በተውኔታችን ውስጥ ጽሀፈ ተዉኔቱ የፈጠረው ቦታ ወይም ድርጊቶችን የሚካሄዱበት ግዜ እና ቦታ መቼት በመባሌ ይጠራል። ፊንታሁን እንግዳ “ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻችው ከ ሀ እስክ ፐ” በተሰኘው መጽሀፉ ላይስለ መቼት እንዲህ ሲል ያስቀምጣል።

> *መቼትን መቼት የሚያሰኘው የድርጊቱ ጊዜ የድርጊቱ ቦታእና ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ ያሉት ማህበራዊ እውነታ ነው። መቼት አጠቃላይ መቼትና ውስን መቼት በመባል በሁለትዐይከፈላል ። አጠቃላይ መቼት በአንድ በተወሰነ የተውኔት ድርሰት ውስጥ የሚገኘው ትልቁ የድርጊቱ*

መከናወኛ የጊዜ መለኪያ እና ትልቁ የድርጊቱ መከናወኛ ቦታ ነው። ውስን መቼት በአንድ የተወሰነ ተዉኔታዊ ድርሰት ውስጥ የሚገኘው ትንሹ የድርጊቱ ጊዜ እና ትንሹ የድርጊቱ መከናወኛ ቦታ ነው።" (ፊንታሁን እንግዲ 1993:11)

ከሀሳቡ እንደምንረዳው መቼት የት ቦታ የተዉኔቱ ታሪክ እንዮተዮረገ የሚያሳይ ነው። እንዱሁም ማህበራዊ እውነታውን ሲባሌ ተውኔቱ የማህበረሰቡን አኗኗር፣ ፖሇቲካዊ ሁኔታን የሚያመሇክት ነው፡

2.3.1 አጠቃላይ መቼት

አጠቃላይ መቼት ማለት በተውኔት ውስጥ ያለው ትልቁ የድርጊት መከወኛ ቦታ ማለት ነው። በተውኔቱ ውስጥ ያሉት ትዕይንቶች ብዙ ጊዜ የሚታዩበት ቦታ አጠቃላይ መቼት ብለን እንጠራዋለን። ፈንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት ድርሰት አፃፃፌ ዘዴ" በተሰኘው መፅሀፉ ስለ አጠቃላይ መቼት እንዲህ በማለት አስቀምጧል።

አጠቃላይ መቼት በአንድ በተወሰነ ድርሰት ውስጥ የሚገኘው ትልቁ የድርጊት መከወኛ ቦታ ነው። ለአስረጅነት ያህል ከታሪኩ ጊዜ አኳያ ክፍለ ዘመኖች ፣ ዓመቶች ፣ ወቅቶች ፣ ወራቶች ፣ሳምንታቶች ፣ ወዘተ ሊሆን ይችላሉ። ከታሪኩ ቦታም አንፃር ፕላኔቶች ፣ አህጉሮች ፣ አገሮች ፣ ከተሞች ፣ ወዘተ እንደየሁኔታው አጠቃላይ መቼት በመሆን ሊቀርቡ ይችላል።(ፋንታሁን እንግዳ ፣ 2005 ፣ 15)

አጠቃላይ መቼት ከላይ እንደተገለጸው ተውኔቱ የሚከወንበት አጠቃላይ የጊዜ እና የቦታ መቼት ነው።ማለትም ተውኔት የሚከወንበት ሀገር ፣ ወረዳ ፣ሰፈር ፣መንደረ ሊሆን ይችላል።

2.3.2 ውስን መቼት

ፋንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፌ ዘዴ" በተሰኘው መፅሀፉ ላይ ስለ ውስን መቼት የሚከተለውን ማብራሪያ አስቀምጧል።ፉንታሁን እንግዳ " የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በሚለው መፅሀፉ ላይ ስለ ገፀ ባህሪያ ሞራላዊ አሳሳል እንዲህ በማለት ገልፆታል።

ውስን መቼት በሌላ በኩል በአንድ በተወሰነ ድርሰት ውስጥ የሚገኘው ትንሹ የድርጊት መከወኛ ቦታ ነው። ለምሳላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በአንድ ቀበሌ ተወስኖ ታሪኩ የሚከናወን ተውኔት ብንፅፍ የዚህ ተውኔት ውስን መቼት ከታሪኩ ጊዜ አኳያ ሳምንታት ፣ ቀናት ፣ሰዓታት ፣ ደቂቃዎች፣ ንጋት ፣ ምሽት ፣ እኩለቀን ፣ ዝናባማ ፣ደመናማ ፣ ፀሀያማ ፣ በጠፍ ጨረቃ

ወዘተ ሊሆን ይችላል። ከታሪኩ ቦታ አኳያም ሳሎን ፣ መኝታ ክፍል ፣ ማድቤት ፣ ቅፅር ገቢ ፣መንገድ ዳር ፣ የንግድ ማዕከል፣ (ፋንታሁን እንግዳ ፣ 2005 ፣ 15)

በአንድ ተውኔት ውስጥ የሚደረጉ ክዋኔዎች ወይም እንቅስቃሴዎች በጥቂቱ የሚከናወንበትን ስፍራ ወይም ትንሹ የድርጊቱ ጊዜና ትንሹ የድርጊቱ መከወኛ ቦታ ዉስን መቼት ይባላል ። በአጠቃላይ ይህ የተውኔት አላባ የሚያሳየን ገፀባህሪያትን በቦታና በጊዜ አማካኝነት የማስተዋወቅ ሀላፊነት (ግዴታ) እንዳለበት ነው። ገፀባህሪያቶቹ ከሚኖሩበት ቦታና ጊዜ ባለፈ ስላሉበት ማህበረሰብ ባህልና የአኗኗር ስልታቸውን ጭምር የማሳወቅ ስራን ይሰራል።

2.4 ገፀ-ባህሪ

ገፀባህሪ ከተውኔት አላባውያን ውስጥ የሚካተት ሲሆን ገፀ_ባህሪያት የገሀዱ አለም ፍጡራን አካልና አምሳል ተለክተው የሚቀረፁ የደራሲው የፈጠራ ወይም ምናባዊ ሰዎች/ነገሮች ናቸው። እነዚህ የደራሲው የፈጠራ ሰዎች ልክ እንደ እውኑ አለም ሰዎች የተሳሉት ገፀባ-ህሪያቶቹ የተውኔቱ ስራ ወደ መድረክ መተርጎም ሲጀመር የተሳሉበትን ባህሪ ተቀብለው መስራት ይጀምራሉ።ፉንታሁን እንግዳ " የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በሚለው መፅሀፉ ላይ ስለ ገፀ ባህሪያ ሞራላዊ አሳሳል እንዲህ በማለት ገልፆታል።

ገፀባህሪ የሚለው ቃል በፈጠራ ታሪክ ውስጥ ያሉትን የድርሰቱን ሰዎች (አበበ፣ ከበደ፣ አልማዝ)፣ በድርሰቱ ውስጥ የተሳሉትን እንስሳት (አህያ፣ ጅብ፣ በግ፣ ቀበሮ)፣ በተውኔታዊ ታሪኩ ውስጥ የሚቀረፁት ሰማያዊ ወይም ሀተታ ተፈጥሮአዊ ፍጥረታትንና መናፍስት (ሰይጣን፣ መላእክት፣ ሰናይ መናፍስት፣እኩይ መናፍስት፣ ጣዕረ መንፈስ) እና ረቂቅ ሀሳቦችን (ተንኮል፣ደግነት፣ መልካም ሰራ፣ ቁንጅና) የመሳሰሉትን ይወክላል። (ፋንታሁን እንግዳ፣ 2009፣ 25)

ገፀ-ባህሪያት የምንላቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ፍጥረታትንና ሀሳባዊ ነገሮችን ይወክላል።

ገፀባህሪያት የሚከውኑት ድርጊቶች በሙሉ በደራሲው አማካኝነት የተሰጣቸውን ነገር በመሆኑ እንደራሳቸው ሳይሆን እንደደራሲው ፍላጎት በመሆን ደራሲው ወደሚመራቸው አቅጣጫ ይጓዛሉ። ‹‹ደራሲው በፈጠረው መቼት ውስጥ እየተንቀሳቀሱ የልበወለዱን ታሪክ የሚከውኑ የአእምሮ ፍጡራን ናቸው›› (ጌታቸው በለጠ፣ 2004፣137) በማለት ያጠናክረዋል።

2.4.1 የገፀ-ባህሪያት አይነቶች

ገፀ-ባህሪያት በተውኔት ውስጥ ባላቸው ሚና እና በባህሪያቸው ምክንያት በታሪኩ ውስጥ ከሚኖራቸው አስተዋፅኦ አንፃር በተለያዩ መልኩ ይከፈላሉ። እነርሱም ወጥና አሰተኔ ፣ አቀንቃኝ፣ ፀረ-አቀንቃኝ፣ ሰናይ፣ እኩይ፣ድብቅ፣ግልፅ፣ታሪካዊና ምናባዊ በመባል ይከፈላሉ። አበይት ገፀባህሪ እና ንዑሳን ገፀባህሪ በመባል ይከፋፈላሉ። ነገር ግን ፊንታሁን እንግዳ “የተዉኔት ድርሰት አጻጻፍ ዘዴ” በተሰኘው መፅሐፉ ላይ እንዲህ ሲል ያስቀምጣል።

“ሰፋ ባለ ትርጓሜ እና አተናተን ሊቀመጡ የሚበቁት አስተኔ እና ወጥ የገጸ ባህሪያት አይነቶች ናቸው” (ፊንታሁን እንግዲ ፣ 1999 ፣ 25) ሲል ያስቀምጣል።

2.4.1.1 ዓብይ/ወጥ ገፀ-ባህሪ

ይህ የገፀባህሪ አይነት ገፀባህሪያቶች በተውኔት ውስጥ ያላቸው የስራ ድርሻ ጎልቶ የሚታይና ለተመልካች በግልፅ ሁኔታ የሚቀመጥ የገፀባህሪ አይነት ነው ‹‹ እነዚህ የገፀባህሪ አይነቶች አካላዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ ማህበራዊና ስነ ምግባራዊ መልካቸው በግልፅ የሚቀርብ ይሆናል›› (የስነ ድራማ መግቢያ፣2003፣ 23)

የገፀባህሪ አይነት ውስጥ የሚመደቡት ገፀ-ባህሪያቶች ተውኔቱ ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ የሚቀጥሉ ናቸው። የነዚህ ገፀባህሪያት ድርሻ በተውኔት ውስጥ ጉልህ ቦታ በተመልካች ዘንድም በባህሪያቸው እና በምግባራቸው የታወቁ ይሆናሉ። ውስብስብ የሆኑ ስሜቶች ወይም የታሪኩን ዋና ክፍል የሚይዙት ወጥ ወይም አበይት ገፀባህሪያት የሚባሉት ናቸው።

ወጥ ገጸ ባህሪያት የምንላቸው በተለያዩ የገጸ ባህሪያት አሳሳል ደረጃ ሲሳሉ ነው። ፊንታሁን እንግዳ“ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ከ ሀ እስከ ፐ በሚለው መፅሀፉ ያስቀምጣል። “ወጥ ገጸ ባህሪ አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ ልበናዊና ግብረ ገባዊ መልኩ ጥልቀት ባለው መንገድ እና ግልጥልጥ ባለ ሁኔታ ተስለው

2.4.1.2 ንዑስ ገፀ ባህሪያት

ሰለ ንዑስ ገፀ ባህሪ የስድስተኛ ክፍል የክወናና ዕይታ ጥበባት የተማሪ መፅሀፍ ላይ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል። "ንኡስ ገጸ-ባህሪያት በ ተውኔት ታሪክ ሊይ ጉልህ ሚና የሌላቸው ታይተው ሊጠፈ የሚችሉና በአንድ ተውኔት ለትንንሺ ጊዜ የሚቆዩ ገፀ ባህሪያት ናቸው። ይህም ማለት በአራቱ የአሳሳል ደረጃዎች እንደማይቀረጹ እና መቀረጽ እንደማይጠበቅባቸው ያሳያል።" (የስድስተኛ ክፍል የክወናና ዕይታ ጥበብ መፅሀፍ ፣ 2014 ፣ 12) በማለት ይገልፀዋል።

2.4.1.3 አቀንቃኝ ገፀ-ባህሪ

ሰለ አቀንቃኝ ገፀ ባህሪ የስድስተኛ ክፍል የክወናና ዕይታ ጥበባት የተማሪ መፅሀፍ ላይ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል።"አቀንቃኝ ገጸ-ባህሪ ከፀረ-አቀንቃኝ ገጸ-ባህሪ በተቃራኒው የተውኔቱን ሰናይ ሀሳብ የሚደግፉ ናቸው። አቀንቃኝ ተውኔት ውስጥ መሌካሙን ሀሳብ ይዞ የሚሄዴ ገጸ-ባህሪ ማሇት ጭብጥ ይዘውሌን የሚሄዴ ገጸ-ባህሪያት ናቸው።" (የስድስተኛ ክፍል የክወናና ዕይታ ጥበብ መፅሀፍ ፣ 2014 ፣ 12) በማለት ይገልፀዋል።

2.4.1.4 ፀረ-አቀንቃኝ ገፀ-ባህሪ

አቀንቃኝ ገጸ-ባህሪያት የ ዋናውን ገጸ-ባህሪ ሰናይ ሀሳብ የሚቃወሙ ናቸው።ጸረአቀንቃኝ ገጸ-ባህሪያት ከተውኔታዊ ጭብጡ ያፈነገጡ ናቸው። ይህንን ሀሳብ የስድስተኛ ክፍል የክወናና ዕይታ ጥበባት የተማሪ መፅሀፍ ላይ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል። "ያቀንቃኙን ገጸባህሪ አላማና ግብ የሚጻረርና ለማደናቀፍ የሚጥር ገጸ-ባህሪ ነው።" (የስድስተኛ ክፍል የክወናና ዕይታ ጥበብ መፅሀፍ ፣ 2014 ፣ 12) በማለት ይገልፀዋል።

2.4.1.5 ሰናይ ገፀ-ባህሪ

ሠናይ ገጸ-ባህሪያት የማህበረሰቡን አመለካከት፣ትክክለኛ እና እውነተኛ የመሳሰሉትን መልካም አሰተሳሰብ ደረጃ የሚቀረጹ ገጸ-ባህሪያት ናቸው። ሞራሊዊ እና ስነ-ልቦናዊየ አሳሳል ደረጃቸዉ ጥሩ እና እዉነታ ላይ የተመሠረተ ነዉ። ይህንን ሀሳብ የስድስተኛ ክፍል የክወናና ዕይታ ጥበባት የተማሪ መፅሀፍ ላይ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል። "ከቃሉ መረዳት እንደሚቻለው መልካም ባህሪ የሚንፀባረቅበት ገጸ-ባህሪ ነው።" (የስድስተኛ ክፍል የክወናና ዕይታ ጥበብ መፅሀፍ ፣ 2014 ፣ 12) በማለት ይገልፀዋል።

2.4.1.6 እኩይ ገፀ-ባህሪ

ሰለ እኩይ ገፀ ባህሪ የስድስተኛ ክፍል የክወናና ዕይታ ጥበባት የተማሪ መፅሀፍ ላይ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል።"እኩይ ገፀ-ባህሪ የምንለው ሙሉ በሙሉ ፀባያቸውና ድርጊታቸው የሰናይ ገፀ-ባህሪ ተቃራኒ የሆኑ የሰናይ ገፀ ባህሪያት ተፃራሪ የሆኑ ናቸው።"(የስድስተኛ ክፍል የክወናና ዕይታ ጥበብ መፅሀፍ ፣ 2014 ፣ 12) በማለት ይገልፀዋል።

2.4.1.7 አስተኔ ገፀ-ባህሪያት

እነዚህ ደግሞ በጣም በተወሰነ ምግባር እና አላማ ልናውቃቸው እንችላለን። በታሪኩ ውስጥ ያላቸው የስራ ድርሻ

ከወጥ ገፀባህሪያት ያነሰ ነው። ፋንታሁን እንግዳ "ተኔታዊ መዝገበ ቃላትና ብያኔዎቻቸው ከ ሀ እስከ ፐ" በሚለው መፅሀፉ ስለ ንዑሳን ገፀ ባህሪያት እንዲህ በማለት ያስቀምጣል። "በየፈጠራ ድርሰት ታሪክ ውስጥ የሚሰጣቸው የተሳታፊነት ድርሻ ትንንሽ ከመሆን አልፎ በአካልም ሆነ በግብር ሳይገኙ በስም ብቻ ተጠቅሶ የሚታለፉበት አጋጣሚ የተፈጠሩ ገፀ ባህሪያት ነቸው።"(ፋንታሁን እንግዳ፣ 2009፣ 30)

ገፀ-ባህሪያት የስራ ድርሻ አናሳ በመሆኑ ምናልባት አንዳንዴ ገፀ-ባህሪያቶቹን በአካል ላናያቸው የምንችልበት አጋጣሚ ሰፊ መሆኑን ያሳየናል። በአጠቃላይ ተውኔቶች ላይ ያሉት ገፀ-ባህሪያት በሁለቱ መንገዶች እንደሚቀርቡ ያሳየናል።

2.4.2 የገፀባህሪ አሳሳል ደረጃዎች

ገፀ-ባህሪያት በእውኑ አለም የሚገኙ ሰዎች ተምሳሌት ወይም ወኪሎች ናቸው። ይህ ውክልና ታአማኒነት ያለው እንዲሆን ገፀ-ባህሪያት በጥንቃቄ መቀረፅ ወይም መሳል አለባቸው። አንድ ፀሀፊ ተውኔት ገፀ-ባህሪያቱን በምናቡ በሚፈጥርበት ወቅት ለገፀባህሪያቶቹ መፈጠር ምክንያት የሆነውን ነገር መሰረት አድርጎ ይቀርፃል። ይህ ማለት መልእክት ማስተላለፍ የፈለገበትን የማህበረሰብ ሁኔታ/ቦታ በደንብ ማጥናት ይኖርበታል ማለት ነው።እነዚህ አራቱ ያሳሳል ደረጃዎች አካላዊ፣ማህበራዊ፣ ስነ ልቦናዊ ና ግብረ ገባዊ የአሳሳል መንገዶች ገፀ ባህሪያት ይሳላሉ። ፋንታሁን እንግዳ "የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ" በሚለው መፅሀፉ ስለ ገፀ ባህሪያት የአሳሳል ደረጃዎች እንዲህ በማለት አስቀምጧል።"ሀረበርት ሀፍነር የተባለው የንድፍ ሀሳብ ሰው የገፀ ባህሪያት የአሳሳል ደረጃዎች አካላዊ፣ማህበራዊ፣ስነ-ልቦናዊና ሞራላዊ የአሳሳል ደረጃዎች ናቸው።(ፉንታሁን እንግዳ፣2009፣26) በማለት ይጠቅሳል።የእነዚህ አሳሳል ደረጃዎች አስፈላጊነት ሰው በነዚህ ነገሮች የታጠረ አካል ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ተውኔቱን በሰዎች ዘንድ ተአማኒነት እንዲኖረው ለማድረግ አስፈላጊ ናቸው።

2.4.2.1 አካላዊ የገፀባህሪ አሳሳል ደረጃ

አካላዊ የአሳሳል ደረጃ የምንለያቸው ገፀ ባህሪያተበአካላዊ ገፅታቸው ነው። ለምሳሌ ረጅም፣ አጭር፣ ቀይ፣ ጥቁር፣ ወፍራም፣ ቀጭን ... ወዘተ ብለን የምንጠራቸው ማለት ነው። ታድያ ይህ የአሳሳል አይነት ብዙ ጥረትን የማይጠይቅ ለተውኔታችን እንዲመቸን አድርገን የምንስለው የአሳሳል ደረጃ ነው።ፉንታሁን እንግዳ " የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ" በሚለው መፅሀፉ ላይ ስለ ገፀ ባህሪያ ሞራላዊ አሳሳል እንዲህ በማለት ገልፆታል። ‹‹ልክ በመንገድ ከሚተላለፉት ሰዎች የአንዱን አቋም ተመልክተን ከምንናገረው የተለየ አይደለም›› (ፋንታሁን እንግዳ፣ 2009፣ 27) ከፋንታሁን ሀሳብ የምንረዳው ውስብስብ ያልሆነ ቀላል የአሳሳል ደረጃ እንደሆነ ነው።

2.4.2.2 ማህበራዊ የገፀባህሪ አሳሳል ደረጃ

ከስሙ እንደምንረዳው ይህ አይነት የአሳሳል ደረጃ የሚያተኩረው ማህበራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ነው። ይህንን

ሀሳብ የስድስተኛ ክፍል የክወናና ዕይታ ጥበባት የተማሪ መፅሀፍ ላይ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል። "ገፀባህሪው ያለበትን ደረጃ ያሳየናል ለምሳሌ ተምሯል አልተማረም፣ አግብቷል አላገባም፣ የሀይማኖት ሁኔታውስ ምን ይመስላል ከሚኖርበት ማህበረሰብ ጋር ያለው ተግባቦት እንዴት ነው የሚሉትን ያጠቃልላል።"(የስድስተኛ ክፍል የክወናና ዕይታ ጥበብ መፅሀፍ ፣ 2014 ፣ 12) በማለት ይገልፀዋል።

ይህንን ለመረዳት ታድያ ልክ እንደ አካላዊ ገለፃ ቀላል አይሆንም። ከውጪ ሆነን ይህ ገፀባህሪ እንዲህ ነው ማለት አንችልም የግድ ገፀባህሪውን በዚህ መንገድ ለማወቅ ተውኔቱን ማየት ይጠበቅብናል።

2.4.2.3 ስነ ልቦናዊ የገፀባህሪ ኣሳሳል ደረጃ

ይህ ደግሞ ትኩረቱን የሚያደርገው ገፀባህሪው በውስጡ ስለሚመላለሱ ወይም ስለሚያስባቸው ጉዳዮች ነው።ፉንታሁን እንግዳ " የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በሚለው መፅሀፉ ላይ ስለ ገፀ ባህሪያ ሞራላዊ አሳሳል እንዲህ በማለት ገልፆታል።

> *የገፀባህሪያትን ልዩ ልዩ ምኞቶች፣ ተስፋዎች የመጥላትና የማፍቀር ስሜቶችንና ሰበበ ድርጊቶች በድምሩ በጭንቅላት ውስጥ ተውጠንጥነው ለውጫዊ አለም የሚሆኑትን ስሜታዊነትንና አስተዋይነትን ሁሉ በመቅረፅ የየገፀባህሪያቱ ህሊናዊ መልክ የሚታይበት መንገድ ነው።(ፉንታሁን እንግዳ፣ 2009 ፣28)*

ገፀባህሪ በዚህ አይነት የአሳሳል ደረጃ ሲሳል ውስጡ ያሉትን ስሜቶች ወደ ተመልካች ማሳየት የሚችልበት መንገድ መፍጠር አለበት።

2.4.2.4 ሞራላዊ የገፀባህሪ የአሳሳል ደረጃ

ይሄኛው የአሳሳል አይነት ልክ እንደ ስነ ልቦናዊ አሳሳል አይነት በውስጥ ሀሳቦች የተሞላ ሲሆን ከሱ የሚለየው ነገር ግን የመከበር እና ያለመከበር ጥያቄዎች ላይ በማተኮሩ ነው።ፉንታሁን እንግዳ " የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በሚለው መፅሀፉ ላይ ስለ ገፀ ባህሪያ ሞራላዊ አሳሳል እንዲህ በማለት ገልፆታል።

> *ተፈጥሮ ከሚፈቅደው በታች ወርዶ ቅጥ ያጣ ስግብግብ ሆኖ ሲቀርብ ወይም ከሚገባው በላይ ክብር ፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም ከሁለቱ በተቃራኒ አለማዊና መንፈሳዊ መመሪያዎችና ህጎችን ተቀብሎ የሞራል አስተማሪና ሰባኪ ሲሆን በሚያሳዩና በመሳሰሉት ፍሬ ሀሳቦች ላይ በማተኮር ገፀባህሪያቶችን ከዚህ አንፃር በመቅረፅ ላይ ያነጣጥራል።*

(ፋንታሁን እንግዳ፣ 2009፣ 29)

ከገለፃው እንደምንረዳው ሞራላዊ የገፀባህሪ የአሳሳል ደረጃ ዋነኛ ትኩረቱ የመሆንና ያለመሆን ከመጠን በላይ አንድ ነገር ላይ ፍላጎት ማሳደር እና እሱን ለማግኘት አጉል የመስገብገብ አይነት ባህሪ ያላቸውና ከመጠን በላይ ሰላማዊ ገፀባህሪያትን የምንቀርፅበት ደረጃ ነው።

2.5 ሴራ

ሴራ በአንድ የተውኔት ታሪክ ውስጥ አንኳር የሚባል የታሪክና የግጭት ጥምር ሲሆን የታሪኩን ድርጊቶች በቅደም ተከተል በምክንያትና ውጤት ላይ ተመርኩዞ የሚያቀርብ የአላባ አይነት ነው ‹‹ ሴራ የምክንያትና ውጤት ትስስር ያላቸውን ተከታታይ ድርጊያዎችና አይነተኛ ጉዳዮችን የሚመለከት መግቢያ መሀከልና መጨረሻ ያለው የድርጊቶች መዋቅር ነው››(የስነ ድራማ መግቢያ ፣2003፣24) በማለት ያስረዳል።

ሴራ የሚለው ቃል ግብሩ የሚሆነው ምን ተደረገ፣ ለምን ተደረገ፣ እንዴት ተደረገ የሚሉትን ሀሳቦች በግልፅ ማስቀመጥ ነ ው። በተውኔት ውስጥ ሴራ የሚባለው አለባ ባይኖር ታሪኩ ሳቢና አጓጊ የመሆን እድሉ በጣም የላላ ይሆን ነበር።የሻው ተሰማ "መሠረታዊ የዘገባ አፃፃፍ ዘዴ" በተሰኘው መፅሀፉ ስለ ሴራ እንዲህ ሲል ያብራራል። ‹‹ የአንድን ጥበባዊ ትረካ ከስር- እጫፍ የሚያያይዝ የታሪክ የውስጥ ለውስጥ ‹‹ፌሮ›› ነው›› (የሻው ተሰማ ፣ 1998፣ 86)

የተቆራረጡ ታሪኮችን እንደሰንሰለት በማያያዝ ተውኔቱን የማጉላት ከፍተኛ ሚና እንዳለው ነው።

በተውኔት መዋቅር ውስጥ እውቂያ ጡዘትና ልቀት የሚባሉትን ደረጃዎች ጥሩ ሆነው ተደራስያን ዘንድ እንዲታዩ ይህ ሴራ የተባለው አላባ ከፍተኛ የሆነ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

2.5.1 የሴራ አይነቶች

ፋንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በሚለው መፅሀፉ ላይ ሴራን በአምስት ይከፍለዋል። "እነርሱም ጥብቅ ሴራ፣ ጥምር ሴራ፣ ልቅ ሴራ፣ ነጠላ ሴራና ሴራ አልባ በመባል ይተወቃሉ።" *(ፋንታሁን እንግዳ፣2003፣40 -41)*

ከነዚህ የሴራ አይነቶች ውስጥ ብዙ ጊዜ ስራ ላይ የሚውሉትንና አጥኚዋ ለጥናቷ ጠቃሚ ናቸው ብላ ያሰበቻቸውን ሁለት የሴራ አይነቶችን ማለትም ጥብቅ ሴራና ጥምር ሴራ የሚባሉትን ሁለት የሴራ ዓይት በዝርዝር ትመለከታለች።

2.5.1.1 ጥብቅ ሴራ

ጥብቅ ወይም አብይ ሴራ የሚባለው ከሴራ አይነቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን ታሪኩ ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ የገፀባህሪያት እንቅስቃሴዎች እና ንግግር በሙሉ በምክንያት እና በውጤት የተደገፈ ነው። ፋንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በሚለው መፅሀፉ ላይ ሰለ ጥብቅ ሴራ እንደሚከተለው ያጠናክረዋል።

> *ባለጥብቅ ሴራ ተውኔት ገፀባህሪያቶቹ (ድርሰተሰቦቹ) በጥንቃቄ የተሳሉ በመሆናቸው እንቅስቃሴአቸው፣ ድርጊታቸውና ንግግራቸው ሁሉ ከአጥጋቢ ምክንያት እና ውጤት ጋር የተቀረፁ የሴራ አይነት ሲሆኑ ከተውኔቱ ታሪክ ጋር ከመጀመሪያው ሀሳብ እስከመጨረሻው አብረው ይዘልቃሉ። (ፋንታሁን እንግዳ፣2003፣41-42)ብዙ ጊዜ በመሪር ተውኔቶች ላይ ይስተዋላል።*

ገፀባህሪያት በተውኔት ውሰጥ ያላቸው እንቅስቃሴዎች በሙሉ በዘፈቀደ የሚመራ ሳይሆን ምክንያት እና ውጤትን መሰረት በማድረግ የሚጓዝ መሆኑን እንረዳለን። ግጭት ለጥብቅ ሴራ መፈጠር አብይ ምክንያት ነው ሁለት የተለያዩ ሰዎች አንድ ነገር ላይ ተመሳሳይ የሆነ ፍላጎት ካሳደሩ ያንን ለማግኘት አንዱ አንደኛውን ለማሸነፍ የሚደረግ ሹኩቻ ሴራን ይፈጥራል።

2.5.1.2 ጥምር ሴራ

ጥምር ሴራ ሌላው ወሳኝ የሴራ አይነት ሲሆን በውስጡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው የተለያዩ አላማዎችንና ግቦችን የያዘ ነገር ግን እርስበርሳቸው ቁርኝት ያላቸው ሴራዎችን በአንድነት ይዞ የሚገኝ የሴራ አይነት ነው። ምንም እንኳን ጥምር ሴራ የራሱ ንኡሳን ታሪኮችና አላማዎች ይዞ የሚራመድ ቢሆንም በስተመጨረሻ ግን ሁሉም ንኡሳን ሴራዎች እንደ የጥብቅ ሴራው አካል እልባት ይፈለግላቸዋል።ማለትም ጥብቅ ሴራ የሚያራምደውን አብይ ርእሰ ጉዳይ አጉልቶ ከማሳየት አልፎ የሚያነሳቸው ንኡሳን ታሪኮች ከአብይ ወይም ጥብቅ ሴራ ታሪክ ጋር ሲነፃፀሩ ጎልቶ መታየት የለባቸውም ምክንያቱም በጥምር ሴራ ስር የሚነሱ ቁርጥራጭ ታሪኮች የጥብቅ ሴራ ታሪክ መጋቢ ተደርገው ስለሚከሰቱ ሲል ይገልፀዋል። (ፋንታሁን እንግዳ፣ 2009 ፣41)

2.6 ቃለ ተውኔት

ፋንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ በተሰኘው መፅሀፉ ላይ ስለ ቃለ ተውኔት እንዲህ በማለት ያስቀምጠዋል።

ቃለ ተውኔት ከተውኔት አላባውያን ውስጥ አራተኛው ሲሆን የቃለ ተውኔት ምግባር በአንድ ተውኔት ውስጥ ያሉት ገፀባህሪያት የሚጠቀሙት (የሚግባቡበት) ቋንቋ ነው። ቃለ ተውኔት ሁለትና ከዛ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ የቃል ምልልስ ሲሆን ቃለ ተውኔት ሲፃፍ በተለያየ መንገዶች ሊፃፍ ይችላል። በግጥም፣ በዝሩው (በስድ ፅሁፍ)ና በዝርውና በግጥም መልክ መፃፍ ይቻላል። ቃለ ተውኔት በአንድ ትልቅ ወይም ትንሽ ድርጊት ምክንያት ሊፈጠር ይችላል።ፉንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በሚለው መፅሀፉ ስለ ቃለ ተውኔት እንዲህ በማለት የገልፀዋል። ‹‹ገፀባህሪ ከድርጊትና ከግጭት እንደሚመነጭ ሁሉ ቃለ ተውኔት ደግሞ ከግጭት ፣ ከድርጊት ፣ ከገፀባህሪያትና ከመቼት ግንኙነት ይፈጠራል። (ፋንታሁን እንግዳ፣2009፣46)

ይህ ገለፃ የሚያሳየን ቃለ ተውኔት ከተዘረዘሩት ውስጥ በአንደኛው ምክንያት ሊፈጠር እንደሚችልና ከእያንዳንዳቸው የተውኔት አላባውያን ጋር ቁርኝት እንዳለው ነው። ቃለ ተውኔት ሲዘጋጅ ለተመልካች ሊገባ በሚችል መንገድ መቅረብ አለበት ምክንያቱም ቃለ ተውኔት ምስል ከሳች መሆን ስላለበት ነው። ፉንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በሚለው መፅሀፉ ስለ ቃለ ተውኔት ከላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ እንዲህ በማለት ያጠናክረዋን።

ቃለ ተውኔት በአንድ ተውኔት ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ በዝርዝር እንመልከት የመጀመርያው ታሪኩ እየተፈፀመበት ያለውን ቦታና ጊዜ በገፀባህሪያቶቹ ቃለ ተውኔት አማካኝነት እናውቃለን። ገፀባህሪያቶቹ ከሰማቸው ጀምሮ እነማን እንደሆኑ የሰራ፣ የኑሮ የመሳሰሉትን ሁኔታዎች ያሳውቀናል። የየገፀባህሪያቶችን ባህሪ ያሳየናል የአሳሳል ደረጃቸውን ያሳውቀናል። የታሪኩ አንዱ አካል የሆኑ ነገር ግን መድረክ ላይ ሊፈፀሙ የማይችሉ ከመድረክ ጀርባ የተከናወኑ ድርጊቶችን በቃለ ተውኔት ምክንያት ምን እንደሆኑ ምን እንደነበሩ ለማወቅ እንችላለን። ከቃለ ተውኔት ጠቀሜታዎች እንደምንረዳው የተውኔቱ ግማሽ አካል በቃለ ተውኔቱ እንደተደገፈ ነው። ቃለ ተውኔት ሲፃፍ ተውኔቱ የሚቀርብላቸውን ሰዎች በደንብ ማወቅ ተገቢ ነው ይህ ካልሆነ ግን በቃለ ተውኔት ማስተላለፍ የተፈለገው መልእክት መና ሆኖ ይቀራል ማለት ነው። በተለይ መተኮር ያለበት ጉዳይ የዕድሜ ደረጃቸው፣ የትምህርት ደረጃቸውና የኑሮ ደረጃቸው ላይ መሆን አለበት። (ፋንታሁን እንግዳ፣2009፣47)

በተጨማሪም በተውኔት ድርሰት ፅሁፍ ውስጥ ስርአት ነጥቦች ቃለ ተውኔትን የማጎልበት ከፍተኛ ሚና

አላቸው ። ቃለተውኔት በተውኔቱ ውስጥ የተገለፁ ገፀ ባህሪያ የሚያደርጓቸው ቃለ ምልልስ ስለሆ በግል ገፀ ባህሪያትን እንዲገልፁ ተደርገው መቀመጥ አለበት።

2.7 ጭብጥ

ጭብጥ ከተውኔት አላባውያ መካከል አንዱ ነው። ጭብጥ በዋናነት በታሪኩ ውስጥ እንዲተላለፍ የተፈለገው ዋና ሃሳብ ወይም መልዕክት ነው። ፉንታሁን እንግዳ “የተውኔት ዴርሰት አጻጻፌ ዘዴ” በሚለው መፅሀፉ ላይእንዲህ ሲል ያስቀምጠዋል። “ጭብጥ የሚነቀሰው ከሴራ፣ ከገጸ ባህሪያት፣ ከቃለተውኔትና ከመቼት ነው።” (ፉንታሁን እግዳ ፣ 2005 ፣61)

ይህም ማለት ሴራ፣ ገጸ ባህሪይ፣ ቃለ ተውኔት፣ መቼት ከሌለ ጭብጥ ሊኖር እንደማይችል እና ጭብጥ ተብሎ እንዲቆም ያደረጉት ልሎች የተውኔት አላባውያን እንደሆኑ ይገለጻል። በአጠቅላይ ጭብጥ የሚነቀሰው ከሴራ፣ ከገፀ-ባህሪያት ፣ ከቃለ-ተውኔት እና ከመቼት ነው።

3. የመረጃ ትንተና

3.1 የሸምጋይ ተውኔት ጭምቅ ታሪክ

የሸምጋይ ተውኔት በእውነቸኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ታሪኩ የሚጀምረው በአለቃ ገብረሃና እና በወ/ሮ ማዘንጊያሽ መኖሪያ ቤት ውስጥ አለቃ ገብረሃና ፀሎት እያደረሱ ነው። ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ወ/ሮ ማዘንጊያሽ ወደ ሳሎን ትመጣለች አለቃ ገብረሃናም ምሽታቸውን ሲያዩ ፀሎታቸውን አቋርጠው በነገር ይለክፏታል። ማዘንጊያሽም የአለቃ ገብረሃና ነገር ስለገባቸው ዝም ብለው ፀሎታቸውን እንዲያደርሱ ትነግራቸውና ወደ ጓዳ ትገባለች አለቃ ገብረሃናም ቁርስ እንድትሰጣቸው ይጠይቋታል። ወ/ሮ ማዘንጊያሽም ምግቡን ታቀርብላቸዋለች፣አለቃ ገብረሃናም ምግቡን ከፍተው ሲያዩት ትንሽ ስለሆነባቸው ሚሽታቸውን በአሽሙር ምግቡ እንደበዛ ይነግሯታል።ወዲያውኑ አለቃ ገብረሀና ወደ አፄ ዮሐንስ ለወጊያ ሊሄዱ እንደሆነ ለሚስቱ ይናገራሉ።ጌታነህም በሚሰራው ስራ ምክንያት ከህዝቡ እንደተገለለ እና ማንም እየቀረበው እንዳልሆነ ይነግራቸዋል።አለቃ ገብረሃናም ምን እንደሚሸራ ቢያውቁም በድጋሜ ከሱ መስማት ስለፈለጉ ስራውን ይጠይቁታል።ጌታነህም ቆዳ እንደሚሰራ ይነግራቸዋል።ከዛም አከታትሎ ህዝቡ ፋቂ እያለ እያንቋሸሸው እንደሆነ እና ከሰው እኩል አለመታየቱ በጣም አሳዝኖት አለቃን ከመንግስት ዘንድ ሂደው ነቆዳ እና የሸመና ስራ የተከበረ እንደሆነና ከሰው እኩል እንደሆኑ እንዲናገሩለት ይጠይቃቸዋል።አለቃ ገብረሃናም በስምህ ካልጠሩህ ማን ብለው እንዲጠሩህ ትፈልጋለህ በማለት ይበሳጩበትና መልሰው እሂ ነገር መቆም ቢችል ኑሮ ቴዎድሮስ አዋጅ ሲናገር ያስቆመው ነበር በማለት ይመልሱለታል።ወዲያውኑ ተክሌ ከውጭ በፍጥነት ይመጣና እየተቻኮለ ወደነ አለቃ ገብረሃና ቤት ብዙ ወታደር እየመጣ እንደሆነ ይነግራቸውና በጥድፊያ ወደ በር ተመልሶ ሊሄድ ሲል አለቃ አስቁመውት እንደገና እርገጠኛ መሆኑን ይጠይቁታል።ተክሌም እርግጠኛ እንደሆነ ነግሯቸው ይወጣል።ወዲያውኑ አለቃ እና ጌታነህ ወደ ቆጥ ተሯሩጠው ይወጡና ይደበቃሉ።እንደተደበቁ በጅሮንድ አሞኜ ጠይቱን ትክሻው ላይ አድርጎ ቤት ይገባል።በጅሮንድ አሞኘም ቤት ማንም አለመኖሩን ሲያይ ትንሽ ከቸቀመጠ በኋላ ተመልሶ ይወጣል።የሱን መውጣት ያዩት አለቃ ገብረሃና ከቆጡ ይወርዱና ወደ በር ሂደው ከፍተው ሲያዩት ተመልሶ መምጣቱን ሲያረጋግጡ በድንጋጤ ጓዳ ይገባሉ።ከዛም በጅሮንድ አሞኜ ጥይቱን ይዞ ቤት ከገባ በኋላ ሙሉ ቤቱን እየዞረ ቢፈትሽ ስላጣቸው አማራጩ መቀመጥ ነበር ወዲያውኑ ማዘንጊያሽ ከውጭ በእስራ ውሃ ይዛ ትመጣለች። በዚህ ጊዜ አሞኜን ስታየው ትደነግጥና በሩቅ ሰላምታ ትሰጠዋለች በጅሮንድ አሞኘም እንስራውን አስቀምጣ እንድትመጣ ይነግራታል እሷም ወደ ጓዳ ገብታ እንስራውን አውርዳ ልትወጣ ስትል አለቃን ከጓዳ ተደብቀው ስታያቸው ተናዳ እንዲወጡ ትነግራቸዋለች በጅሮንድ አሞኘም በአለቃ ገብረሃና መደበቅ ይገረምና እንዲወጡ ትዘይጠይቃቸዋል።አለቃም ከጓዳ ይወጣሉ ከዛም በጅሮን አሞኜ በማስፈራራት ለአሐቃ ትዕዛዝ ያዝዛቸውና ሊወጣ ሲል አዋጅ ሲነገር ይሰማል በዚህ ጊዜ በጅሮንድ ተናዶ ይሄዳል።ወዲያውኑ ጥሩነሽ እና ተክሌ ወንበር ተክለው የቅፀላ

ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ገብረሃና ከርቀት ሲያዩዋቸው በመደሰት በመሃል ያቋርጣቸውና ጥሩነሽን ይሉካታል።ጥሩነሽም ወዲያውኑ በፍጥነት ተመልሳ ያየችውን ነገር ሁሉ ለአለቃ ታስረዳቸዋለች።አለቃም ለመደበቅ እየተሯሯጡ እያለ ወታደር ወደቤታቸው ይገባል።ወታደሩም ለአለቃ ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ ተልኮ እንደመጣ ይነግራቸዋል።ጠብረሃናም ሀሳባቸውን እንደማይቀይሩና ከነሱ ጋር እንደማይሰሩ በተለይ የሸዋውን ንጉስ ሚኒሊክን አብዝተው እንደሚደግፉ ይነግሩታል።በዚህ ጊዜ ወታደሩም ተናዶ ተበጃውን ከአለቃ ግንባር ላይ ሲደቅንባቸው ጥሩነሽና ጌታነህ በፍራት ይወድቃሉ።በድጋሜ ወታደሩ ገብረሃናን ሲጠይቃቸው ሃሳባቸውን እንደማይቀይሩ ነግሩታል በዚህ ጊዜ ወታደሩ እንደሚገላቸው ነግራቸዋን። አለቃም ምንም ቢመጣ እንደማይፈሩ እነገሩት እያለ ከውጭ በተተኮሰ ጥይት ወታደሪ ተመትቶ ይወድቃል።ገብረሃናም ተደስተው ማን እንደገደለው ለማየት ዘደ በር ሲሄዱ ተክሌ ጥይቱን ይዞ ይገባል።በዚህ ጊዜ አለቃ በጣም ተደስተው ያቅፋታል።

3.2 የተውኔት አላባውያ ትንተና

3.2.1 የሸምጋይ ተውኔት የመቼት ትንተና

3.2.2 የሸምጋይ ተውኔት አጠቃላይ የመቼት ትንተና

የመቼት ትንተና የምንለው በምዕራፍ ሁለት እንደተመለከትነው መቼት የሚባለው የተውኔት አላባ በተውኔት ውስጥ ያለው ሚና ገፀባህሪያት የሚኖሩበትን ዘመንና ድርጊቱ የሚካሄድበትን ቦታ የሚጠቁም እንዲሁም ማህበራዊ እውነታዎችን የሚያሳይ ነው። መቼት የሚለው ቃል የመጣው ‹‹መቼ›› እና ‹‹የት›› ከሚሉት ቃላት ነው። መቼትን መቼት የሚያሰኘው የድርጊቱ ጊዜ የድርጊቱ ቦታእና ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ ያሉት ማህበራዊ እውነታ ነው። መቼት አጠቃላይ መቼትና ውስን መቼት በመባል በሁለት ይከፈላል ። የሸምጋይ ተውኔት አጠቃላይ የቦታ መቼት ብለን ስንመለከተው አጠቃይ የቦታ መቼቱ በጎንደር አካባቢ የተፈፀመ ነው። ይህም ታሪኩ ሌላ ውስን የቦታ መቼት የሌለው ሲሆን ታሪኩ ከመጀመሪያው ትዕንት እስከ መጨረሻው ትዕይንት በአለቃ ገብረሃና መኖሪያ ቤት የተፈፀመ ነው። የሸምጋይ ተውኔት አጠቃላይ የጊዜ መቼቱ በግፅ ባለመቀመጡ ምክንያት ተውኔቱን በማንበብ አጠቃላይ መቼቱን መግለፅ ችላለች። በመሆኑም አጠቃላይ የጊዜ መቼቱ ከቃለ ተውኔቱ መረዳት እንደተቻለው ከ1934 ዓ.መ እስከ1936 ዓ.ም መሆኑን አጥኚዋ ከተውኔቱ ላይ ከተገለፁት ቃለ ተውኔት እና ከተወከሉት ገፀ ባህሪያት ለመረዳት ችላለች።

3.2.3 የሸምጋይ ተውኔት ውስን የ መቼት ትንተና

በምዕራፍ ሁለት እንደተመለከትነው ውስን የጊዜ መቼት ማለት ውስን መቼት በሌላ በኩል በአንድ በተወሰነ ድርሰት ውስጥ የሚገኘው ትንሹ የድርጊት መከወኛ ቦታ ነው። ለምሳላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በአንድ ቀበሌ ተወስኖ ታሪኩ የሚከናወን ተውኔት ብንፅፍ የዚህ ተውኔት ውስን መቼት ከታሪኩ ጊዜ አኳያ ሳምንታት ፣ ቀናት ፣ሰዓታት ፣ ደቂቃዎች፣ ንጋት ፣ ምሽት ፣ እኩለቀን ፣ ዝናባማ ፣ደመናማ ፣ ፀሀያማ ፣ በጠፍ ጨረቃ ወዘተ ሊሆን ይችላል።

የሸምጋይ ተውኔት ውስን የጊዜ መቼት የሚገልፅ በተውኔቱ ውስጥ ባይጠቀስም አጥኚዋ ተውኔቱን ከትአትር አላባውያ አንፃር ስለምታጠና ውስን የጊዜ መቼቱን ከቴአትሩ ለመውሰድ ችላለች። ስለሆነም ሸምጋይ ተውኔት ዘወትር ሀሙሽ ከቀኑ 11:00 እስከ ምሽቱ 1:00 በብሔራዊ ቴአትር ስለሚቀርብ አጥኚዋ ውስን የጊዜ መቼቱን ከትአትሩ ለመውሰድ ችላለች። ውስን የጊዜ መቼቱን ደግሞ አሁን ላይ ሸምጋይ ተውኔት በብሔራዊ ትአትር ቤት ዘወትር ሀሙስ ከምሽቱ11.:00-1:300 እየተሰራ ስለሆነ አጥኚዋ ውስን የጊዜ መቼቱን ከትያትሩ ለመውሰድ ችላለች። የሸምጋይ ተውኔት ውስን የጊዜ መቼቱ አንድ ቦታ ላይ የተካሄደ ሲሆን ይህም በአለቃ ገብረሃና መኖሪያ ቤት ውስ ነው።

3.3 የገፀ-ባህሪያት ትንተና

3.3.1 የሸምጋይ ተውኔት ወጥ ገፀ-ባህሪያት

ወጥ ገፀ ባህሪያት የምንለው በምዕራፍ ሁለት እንደተመለከትነው ይህ የገፀባህሪ አይነት ገፀባህሪያቶች በተውኔት ውስጥ ያላቸው የስራ ድርሻ ጎልቶ የሚታይና ለተመልካች በግልፅ ሁኔታ የሚቀመጥ የገፀባህሪ አይነት ነው ‹‹ እነዚህ የገፀባህሪ አይነቶች አካላዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ ማህበራዊና ስነ ምግባራዊ መልካቸው በግልፅ የሚቀርብ ሲሆኑ ከአራቱ የገፀ ባህሪያት የአሳሳል ደረጃዎች ተስለው እናገኛቸዋለን።"በሸምጋይ ተውኔት ውስጥ ያሉት ወጥ ገፀ-ባህሪያት አለቃ ገብረሃና፣ወ/ሮ ማዘንጊያሽ ፣ተክሌ ገብረሃና ፣ ጥሩነሽ ገብረሃና፣ ጌታነህ፣ በጅሮንድ አሞኜ እና ወታደር ናቸው እነዚህ ገፀ-ባህሪያት አራቱን የገፀ ባህሪያት አሳሳል ደረጃዎች አሟልተው ይገኛሉ።

3.3.1.1 የአለቃ ገብረሃና አካላዊ አሳሳል ደረጃ

ስለ አአለቃ ገብረሃና በአካላዊ አሳሳል ደረጃ ላይ ግልፅ የሆነ መረጃ የተቀመጠ ሲሆን ቀአንዳንድ ቃለ ተውኔቶች ላይ የተቀመጡ መረጃዎች በግልፅ ለመሳየት ተሞክሯል። ይህም ማለት አለቃ ገብረሃናን ለማሳየት በቃለ ተውኔትም ሆነ በድርጊትገለፃዎች ላይ በበቂ ሁኔታ እንደተቀመጠ ያሳያል። አጥኚዋ በትቂቱ የተመለከተችውን ታሳያለች።

ገፅ- 7:- ገብረሐና:- አቅም አነሰህ ነው አግቦው? ለነገሩ ልክ ነሸ እኔ አቅም ስሌሌኝ ነው ሌላ

ያመጣሸ ያሰኝሻል።

ማዘንጊያሸ:- ኧረ ይተዉ አንቱዬ አርፈው የማይናገረውን ይብሉ።

ገብረሐና:- ብቅ በይማ አንደ'ዜ። ሻሼን ትቻታለሁ - ወድቃ ትቅር። ...

ማዘንግዬ?... የጃንሆይን አዋጅ ሰማሸውም እይደል ቅድም? ከሠሞኑ መሠንበቻዬን መንገድ

እገባለሁ።

ማዘንጊያሽ፡- /ተጣድፋ ከማጀቱ እየወጣች/ “መሰንበቻዬን”?

ይህም መግለጫ እንደ አጠቃላይ የአለቃ ገብረሃናን አካላዊ አሳሳል ደረጃን ይገልፃል። አለቃ ገብረሃና አቅማቸው የደከመ፣ ቀጭን፣አጭር ቁመና እና ቀይ መልክ ያላቸው ሲሆኑ በእጃቸው ላይ መቋሚያ የማይለቁ ፣ጭራ በእጃቸው የሚይዙ፣ሻሽ የሚጠመጥሙና ቀሚስ የሚለብሱ እንዲሁም ሸበት የቀላቀለ ፂም ያላቸው እንደሆነ ያስረዳናል።በተጨማሪም አጥኚ ገፀባህሪያቶችን የሳለችው በአብዛኛው ቴአትሩን በመመልከት ስለሆነ በግልፅ የገፀ ባህሪያቶቹ ማንነት ለመረዳት ትላለች።

3.3.1.2 የአለቃ ገብረሃና ማህበራዊ አሳሳል ደረጃ

አለቃ ገብረሃና ማህበራዊ አሳሳል ስንመለከት በቅስና ትምህት የተማሩ ፣ ማዘንጊያሽ የምትባል ሚስት ያላቸው፣ሁለት ልጅ ሲኖራቸው በኑሮ ደረጃ መካከለኛ የተባለ የኑሮ ደረጃ የሚኖሩ እና በቤተክርስቲ አገልግሎ ከከቄሳውስቱ ጋር በመጣላታቸው ምክንኒያት ከቅድስና የተገለሉ እና በማህበረሰቡ እና በመንግስታቶቹ የተወደዱ ሲሆኑ ነገር በማጣመም እና ሸሙጥ በመናገር የሚታወቁ ናቸው። አለቃ ገብረሀና ቤታቸው ሰው እንዳይመጣባቸው የሚፈልጉም ጭምር ናቸው። በተለይ አለቃ ገብረሃና በማህበረሰቡ እና በመንግስ ሸሞች መካከል ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸው ሰው ሲሆኑ ብዙውን ጊዜ ትንቢት ተናጋሪ አድረገው ይመለከቷቸዋን።

ገፅ-12፡-ጌታነህ፡- ፊት ከእፍርታም አገርዎ ጋር ያስታርቁኝ።

ገብረሐና፡- እኔ ሆይ?

ጌታነህ፡- መቼም ከእስዎ ሌላ የሁሉን ልብ ያማለለ የለ ዘንድሮ።

ገብረሐና፡- እንዴት ጃል?

ጌታነህ፡- ከንጉስ እስከ ገባሪ፣ ከደገኛ እስከ ቆለኛ አንድም በችሎት ችሎታዎ፣ አንድምባቋቋም ፈጠራዎ፣ ደግሞም በተሸጋሪ ጨዋታዎ ታዋቂ ነዎ። አገር ይሰማዎል።አገር ይታዘዝዎል። ንጉስ ይፈራዎታል። ዝም አይበሉን። እና ... እግዚሃርቢያሳይዎ፣ መላኩ ቢያመላክትዎ ለምንድን ነው አገርዎ እምትጠየፈኝ አለቃ? ለምንድን ነው እምትገፋኝ? ለምንድን ነው ፋቂ›› እምትለኝ?!

3.3.1.3 የአለቃ ገብረሃና ስነ ልቦናዊ አሳሳል ደረጃ

አለቃ ገብረሃና የስነ ልቦናዊ አሳሳል ደረጃ ስንመለከት ልጆቹን የሚወዱ የሀገራቸውና ለመንግስታቸው የሚጨነቁ፤ሚስታቸውን የማያምኑ አጥብቀው የሚጠራጠሩናቸው።

ገፅ-9፡- ተክሌ፡-ያ ፋቂው ሰውዬ!

ገብረሐና፡-ምን ልሁን ነው ሚለው?

ተክሌ፡- "ልግባ ወይ" ይላል። "ግባ" ልበለው?

ገብረሐና፡-እናትህን የሚያውቅ ነው ብለህ?

ከቃለ ተውኔቱ መረዳት እንደሚቻለው አለቃ ገብረሃና ሚስተቸውን አለማመናቸው ተጠራጣሪ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።በቅስና ትምህርታቸው ሊቅ ቢሆኑም ከቀሳውስቶች ጋር መጣላት እናመጋጨትየሚወዱእንዲሁምከተለመደውየቅኔወጥተው ለየት ያለ የቅኔ ቅፀላ የሚወዱ ናቸው።

ገፅ-18፡-ጥሩነሽ፡- ኧረ አባ በደንብ እየቀጸልኩ ነው።

ገብረሐና፡- ታዲያ ምን ኾነሀል?

ተክሌ፡- ኧረ ጎንደሬዎች ዝማሜዎን ያልወደዱልዎ እንጂ

ጥሩነሽ፡-እኔም ሰምቻለሁ እሱንስ።

ገብረሐና፡- እንዴት?

ተክሌ፡- እንጃላቸው፡። ከሊቃውንቱ ተርፎ ተማሪው ሁላ እየነቀፈው ነው።
ጥሩነሽ፡- ጉባዔ ቤቶች ሁላ እየከለከሉት እንደሆነ ነው እሚባል።

ይህም ማለት ቃለተውኔቶቹ እንደሚያሳዩ አለቃ ገብረሃና በቤተ ክርስቲያ ያልተለመደ እና ወጣ ያለ ትምህትትን ማስተማር የሚወዱ ናቸው። አለቃ ገብረ ሃና ከሀገር መሪዎች ጋር አብረው መዋል እና ጓደኛ መሆን የሚወዱ። ሀገራቸውን የሚያከብሩ ናቸው። አለቃ ገብረ ሃና የቅስና ትምህርትን ከተለመደው የዝማሬ እና የቅኔ ስርዓት ወጣ ብለው ማቅረብ የሚፈልጉ እንዲሁም ከቄሳውስቶች ጋር መጣላት የሚያስደስታቸው ሰው ናቸው። አለቃ ገብረ ሃና ሚስታቸውን የማያምኑ ሰው ቤት ውስጥ በገባ እና በወጣ ቁጥር ሚስታቸውን የሚያወራባቸው የሚመስላቸው ናቸው።

3.3.1.4 አለቃ ገብረሃና ሞራላዊ አሳሳል ደረጃ

አለቃ ገብረሃና ለሚስታቸውና ለቄሳውስቶች ክብር የማይሰጡ ሰው ናቸው። እንዲሁም ሲናገሩ የሌሎችን ክብር የማይጠብቁ የማጨነቁ ሰው ናቸው።

> *ገፅ-19:-ገብረሐና:- አዛኜን! /በደስታ እየዘለለች ወጣች። ወደ ታችኛው መስኮት ቸኩለው ወሰዱትና/ ና እስኪ ወዲህ። አየኸው ያን ሸንበቆ? አየኸው? እየውማ። ... እርቡቅ አለ ወደ*
>
> *ምድር። ቀና አለ ላንፋውን በሞገስ ዘርግቶ። ወደ ግራ ዘመመ በዝግታ። ወደ ቀኝ*
>
> *መለሰ አለ እንደገና። አየኸው? /አለቃ መቋሚያቸውን አነሱ፣ ተክሌ ዘንጉን*
>
> *አመጣ፣ ሁለቱም በቀኝ እጃቸው ተመረኮዙ፣ ግራ እጃቸውን እንደ ጸናጽል ሸረቡ፣*
>
> *ፊትና ፊት ሆኑ። በዝማሜ ጀምረው፣ ንዑስ መረግድ አስከትለው፣ ድርብ መረግዱ*
>
> *ላይ ደረሱ። የሠሎሞንን ምቅናይ ማዜም ሲጀምሩ የአሁን ካህናት ጥንግ ድርብ*
>
> *ለብሰው አብረው ማዜም ይጀምራሉ.../ እኾኾእ ... ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ያ ከናፍሪሁ*
>
> *ጽጌ ከናፍሪሁ ጽጌ እለ ያውጎዛ ከርቤ እኾኾእ ... ከርሠ ሰሌዳ ከመ ቀርነ ኔጌ። ...*
>
> *እኾኾእ. ... /መቋሚያዎቻቸውን እኩል ሰብቀው፣ ድምጻቸውን እኩል አድምቀው*
>
> *እየዘመሙ ሳለ ጥሩነሽ ድንገት በሩን ከፍታ እያነፈነፈች ገባች። አለቃና ተክሌ*
>
> *አቋርጠው ባይናቸው ምነው አሏት።*

እንዲሁም አለቃ ገብረሃና የሀይማኖት አሰተማሪ እና ሰባኪ ሰው በመሆናቸው ልጇቻቸውን በቅስና የመንፈሳዊ ትምህር የሚያስተምሩ ናቸው። አለቃ ገብረሃና የቤተክርስቲያን ቀሳውስት ያፀደቁትን የቅፀበላ ህጎች ማፍረስ የሚወዱ እና በእነሱ ህጎችና መመሪያዎች መመራት የማይፈልጉ ለቀሳውስቶች ክብር የማይሰጡ ሰው ናቸው። አለቃ ገብረ ሃና ቤተክርስቲያን የማይሄዱ እና የቅዳሴ እና የቅፀላ ስነ ስርዓቱን ቤታቸው ውስጥ የሚሰጡ ህግና ስርዓትን የማያከብሩ ሰው ናቸው።

3.3.1.5 የማዘንጊያሽ አካላዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል

ማዘንጊያ አካላዊ አሳሳል መካከለኛ የሰውነት ውፍረት ያላት፣ ፀይም መልክ እና ፀጉራን በሻሽ የምጠመጥም

እንዲሁም ቀሚስ የምትለብስ ናት። ማዘንጊያሽ ጠንካራ እና ጉልባት ውሃ በቀላሉ በእንስራ በጀርባዋ አዝላ የምታመላልሰ ናት።

ገፅ-8፡-ማዘንጊያሽ፡- ኧረግ ወዲያ!! ... አምሮብዎ ሞቷል።

/በንዴት አንጀቷ ተሰቦ ወደጓዳ ዘለቀች። ማዘንጊያሽ ወደ ጓዳ ስትግባ እሳቸውም ወደ ቃል ጸሎቸው

ተመለሱ። ቀና ብለው ሸቅብ ወደ እግዜር።

ገብረሐና፡-ይልቅ እሳቱን ተይውና ባይሆን በቅሎዬን ቶሎ አሰጭኝልኝማ ጠይዋ ሳትጠመርር

ወደ ቆላ ደርሼ ልመለስ።

ማዘንጊያሽ፡- አሸከርነቱ የሰዎ። ራስዎ ቢያዝዙት ምነው እንዲያው!

/የመንጠቅ ያክል ኮርቻውን ከግድግዳው አውርዳው ወደ እዳሪ ወጣች። እርሷ ከዐይን ስትጠፋ

እና አለቃ ወደ ማጀት ዘለው ሲገቡ አንድነት ኾነ። ብዙም ሳትቆይ ማዘንጊያሽ እያተናነተች

ተመለሰች። ብታጣብርም አለቃ የሉም/

ይህም መግለጫ ወ/ሮ ማዘንጊያሽን በጣም ቁጡ መሆኗን ያመለክታል። ከዚህ በተጨማሪ አጥኚዋ የማዘንጊያሽን አካላዊ አሳሳል የሳለቻት ቴአትሩን በማየት ነው። ወ/ሮ ማዘንጊያሽ ቁመቷ ከአለቃ ገብረሃና የምትበልጥ ቁመና ሲኖራት አጭር ፀጉር አላት።

3.3.1.6 የወ/ሮ ማዘንጊያሽ ማህበራዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል

ወ/ሮ ማዘንጊያሽ ያገባች ስትሆን በኑሮ ደረጃ መካከለኛ የሚባል ኑሮ የምትኖር እና ሁለት ልጆች ያላት ናት። ማዘንጊያሽ ለባሏ ክብር የሌላት እንዲሁም በስዓት ለባሏ የተጠየቀችውን የማትመልስላቸው ስትሆን ለሌሎች ሰዎች ልዩ ክብር ያላት ናት።

ገፅ-5፡-ማዘንጊያሽ፡- እኔ ሂያጅ እስዎም አልተባሉ።

ገበረሐና፡- ታዲያ ምን ያስጐበድድሻል?ማዘንጊያሽ፡- ሳጎበድድ ውዬ ሳጎበድድ ባድር ምን ጨነቀዎ?ገብረሐና፡-ስትጨነቂ አስጨነቅሽኝ እኮ ማዘንጊዬ።

ማዘንጊያሽ፡- ኧረ እኔስ ከጠሎትዎ እንዳላሰታጉልዎ ብዬ እንጂ

ማዘንጊያሽ ከባላቸው ጋር የማይስማሙ እና በባሏ ላይ ውሸማ መያዝ የምትወድ ናት። ወ/ሮ ማዘንጊያሽ ከባሏ ጋር ፍቅ እና ጥሩ ማህበራዊ ግንኙት የሌላት። እንዲሁም የሁለት ልጆች እናት ናት። ማዘንጊያሽ ውሃ ከእሩቅ አካባቢ የምታመላልስ እና የዕለት መጠጣቸውን ለልጆች የምታቀርብ ናት።

3.3.1.7 የወ/ሮ መዘንጊያሽ ስነ ልቦናዊ አሳሳል

የወ/ሮ ማዘንጊያሽ ለባሏ ብዙም ፍቅር የሌላት እንዲሁም አሸሙር መናገር የምትወድ ናት። ወ/ሮ ማዘንጊያሽ አለቃ ገብረሃና ሌሎችን ሲያደንባት የማትወድ ሰው ናት። ወ/ሮ ማዘንጊያሽ በባሏ ላይ መቀለድ የሚያስደስታት እና ከባሏ ውጭ ሌላ ሰውን መንከባከብ የምትወድ ሰው መሆኗን አጥኚዋ ቴአትሩን በምትመለከትበት ጊዜ በምታደርጋቸው ድርጊቶች መረዳት ችላች። እንዲሁም ከዚህ በተጨማሪም ከቃለ ተውኔቱ በመነሳት የወ/ሮ ማዘንጊያሽን ስነ ልቦናዊ አሳሳል መሳል ችላለች።

ገፅ-፡-6፡-ማዘንጊያሽ፡- አይ አፈር በኾንኩት እውነቱን እኮ ነው። አገሬው ሁላ ፋቂ አንጥረኛ እያለ ማን ከደጃፉ አድርሷቸው። የበሉበትን እና የጠቱበትን እንኳን እየተጠየፉ ይጥሉት የለ።

ገብረሐና፡-አይ ማዘንጊያሽ ለእኔ ነው እንጂ ለሌላውማ ማወቅ ትችያለሽ።

ማዘንጊያሽ፡- አንቱ ሰው እኔን ለቀቅ ያርጉኝ!

ይህም ቃለ ተውኔት የሚያሳየው ማዘንጊያሽ ሌላ ሰው ቤት ሲመጣ ተጣድፋ ምግብ እንደምታቀርብላቸው እና ከባሏ የተለዬ እንክብካቤ ለሌሎች ሰዎች መስጠት የምትወድ ሰው መሆኗን ነው። እንዲሁም ወ/ሮ ማዘንጊያሽ ሌላ ሰው ለማግኘት ስትል ከቤት መቀመጥ የማትወድ ሰው ናት። ማዘንጊያሽ ከባሏ ውጭ ሌላ ሰው ቤታቸው ሲመጣ መንከባከብ እና ማውራት የምትወድ ናት።

3.3.1.8 የወ/ሮ ማዘንጊያሽ ሞራላዊ አሳሳል

ሞራላዊ አሳሳል ማለት በምዕራፍ ሁለት እንደተመለከትነው ተፈጥሮ ከሚፈቅደው በታች ወርዶ ቅጥ ያጣ ስግብግብ ሆኖ ሲቀርብ ወይም ከሚገባው በላይ ክብር ፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም ከሁለቱ በተቃራኒ አለማዊና መንፈሳዊ መመሪያዎችና ህጎችን ተቀብሎ የሞራል አስተማሪና ሰባኪ ሲሆን በሚያሳዩና በመሳሰሉት ፍሬ ሀሳቦች ላይ በማተኮር ገፀባህሪያቶችን ከዚህ አንፃር በመቅረፅ ላይ ያነጣጥራል፡፡ ወ/ሮ ማዘንጊያሽ ስግብግ እና ለባሏ ማብላት የማትወድ እንዲሁም ከሚባለው በላይ ባሏ እንዲያከብራት የምትጥር ሰው ናት። እንዲሁም በባሏ በህጎች እና በመመሪያዎች የማትመራ ሰው ናት።

ገፅ-6፡-ማዘንጊያሽ፡- ኧረግ ወዲያ!! ... አምሮብዎ ሞቷል።/በንዴት አንጀቷ ተሰቦ ወደጓዳ ዘለቀች። ማዘንጊያሽ ወደ ጓዳ ስትግባ እሳቸውም ወደ ቃል ጸሎቸው ተመለሱ። ቀና ብለው ሸቅብ ወደ እግዜር።/

ገበረሐና፡- ወይ ሰራህ! እንዲያው ቅል ድንጋይ በሚያደቅበት በዚህ ዘመን ባትፈጥረኝ ምን ይውጠኝ ኖሮ? ይኸው ከመይሳው በፊት ፈጥረህ፣ እሱ ሞቶ እኔን ቋሚ ስታደርገኝ ወይ አንተ ወይ ሰራህ።

/ቁራሽ እንጀራ ያውም በድቁስ ያውም በትንሽ ቆለምሸሸ እያሰቀመጠችላቸው።/

ማዘንጊያሽ፡- ይኸው።

አለቃ ገብረሃና :- ምንድነው እሂ?

ማዘንጊያሽ፡- አነሰ ማለትዎ ነው /ትሰቃለች/ አነሰ ብለው ማሸሟጠጥዎ እንዳይኾን?

ወ/ሮ ማዘንጊያሽ ለባሏ ምግብ እንካን ማቅረብ የማትፈልግ እና ባሏን የማታከብ ሰው ናት። ወ/ሮ ማዘንጊያሽ ባሏን ከሌሎች ሰዎች አሳንሳ/ ዝቅ አድርጋ የምታይ ናት። ይህም አጥኚዋ ተውኔቱን ስታነብ የወ/ሮ ማዘንጊያሽን ሞራላዊ አሳሳል ሊገልፅላት ስላልቻለ ቴአትሩን በመመልከት ወ/ሮ ማዘንጊያሽሽ የምታደርጋቸውን የሰውነት እንቅስቃሴ እና ድርጊት በማየት ሞራላዊ አሳሳሏን ለመሳል ችላለች።

3.3.1.9 የተክሌ አካላዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል

ተክሌ ወጣት፣ቀጭን የሰውነት አቋም ያለው ሲሆን ቀይ መልከመልካም እና መካከለኛ ቁመት ያለው ነው። ተክሌ ቡላ ሱሪ እና ከላይ ፎጣ የሚለብስ ነው። ተክሌ መፅሀፍ ሁልጊዜ በእጁ የሚይዝ ሲሆን አንዳንዴ ጥይት ይይዛል። ይህንን የተክሌን አካላዊ አሳሳል ከቃለ ተውኔቱ በመነሳት ለመሳል ችላለች።

3.3.1.10 የተክሌ ማህበራዊ አሳሳል

ተክሌ ታናሽ በቅስና ትምህ እየተማረ ያለ ሲሆን በተይ ከእረኞች ጋር በጣም የሚዋደድ እና ብዙውን ጊዜ ከእረኞች ጋር አብሮ የሚውል ነው። ተክሌ ያላገባ እና ከቤተሰቦቹ ጋር የሚኖር ነው።

3.3.1.11 የተክሌ ስነ ልቦናዊ የገፀ ባህሪ አሳሳል

ስነ ልቦናዊ ማለት በምዕራፍ ሁለት እንደተመለከትነው የገፀባህሪያትን ልዩ ልዩ ምኞቶች፣ ተስፋዎች የመጥላትና የማፍቀር ስሜቶችንና ሰበበ ድርጊቶች በድምሩ በጭንቅላት ውስጥ ተውጠንጥነው ለውጫዊ አለም የሚሆኑትን

ስሜታዊነትንና አስተዋይነትን ሁሉ በመቅረፅ የየገፀባህሪያቱ ህሊናዊ መልክ የሚታይበት መንገድ ነው። ተክሌ በጣም አሰተዋይ ሲበዛ አባቱን የሚወድ ፣ አሰተዋይ ለሚፈጠው ችግር አስቀድሞ መፍትሄ መፈለግ የሚወድ ሰው ነው።

ገፅ-19:- ተክሌ፡-እኔ ልዕልና ነው እምል። ጥበብ። /እንዴት እንደሚያዳንቀው ተቸገረ/ በቃ …

አቋቋሙ እሚያስደምም፣ ነፍስን ከሠባቱ ሠማያት የሚያደርስ፣ ልብን እሚልስ ነው ባይ ነኝ።

ገብረሐና፡-/ደስ ደስ አላቸው/ አዛኜን?

ተክሌ፡-አዛኜን! ሌላው እምቢ እንዳለ ቢቀር እንኳን፣ የነፍስ ጥበብ መሆኑን ነው ልቤ እሚለኝ፤ ፍቃድዎ ቢኾንማ ቢያስጠኑኝ ነበር ደስታዬ።

ጥሩነሽ፡-እኔም ባጠናው ደስ ይለኛል።

ተክሌ፡- ብቻግን ተከልክሏል ያው …

ይህም ቃለ ተውኔት የሚያሳየው ተክሌ የቅስና ትምህርት የሚወድ እና ለህግና ደንብ ተገዥ የሆነ ነው። በተለይ አለቃ ገብረሃና በቤተ ክህቱ ዘንድ የተከለከሉ ቅኔዎችን ማቅረብ የሚያስደስታቸው ቢሆን ልደጃቸው ግን እሂንን ህግ እንደ አባቱ መጣስ አይወድም። ስለዚህ ተክሌ ህግችን ማክበር የሚያስደስተው ሰው ነው።

3.3.1.12 የተክሌ ሞራላዊ አሳሳል

ተክሌ በመፈሳዊ የትምህርት አገልግሎ የተሰማራ እና አህቱን የቅስና ትምህርት ማስቀፀል የሚተባበር ደግ ስራን አዘውትሮ የሚሰራ ሰው ነው። ተክሌ አባቱ አለቃ ገብረሃናን የሚያከብር እና ለአባቱ መከታ የሆነ የአባቱን ጠላቶች የማይወድ እና *መበቀል የሚወድ ሰው ነው።*

ገፅ-16:-ይሁን፡-ዙሪያችን ጠላት ከቦን ስመለከት ከቅኔው ይልቅ ይሄ ይጠቅመን ይሆን ብዬ ነዋ።

ገብረሐና፡-እሱስ እውነትህን ነው … ጥበብ በተናቀበት ሀገር … ገዢው ጥይት ይሆናል።የኾነስ ኾነና መታኮሱን ትችልበታለህ?

ይሁን፡-አንድ ታጣቂ አሳይቶኛል …

ገብርሐና፡-የሆነ ሆኖ ከጥይት ይልቅ ቅኔው ይሻልሀል፡

:ይሁን፡-ሁለቱንም መያዝ አይከፋም። ጠላትችን ለመበቀል ያግዛል።

ከዚህ ቃለ ተውኔት መረዳት እንደሚቻለው ይሁን የአባቱን ጠላቶች መበቀል እና አባቱን የሚጠብቅ ለአባቱ ትልቅ ክብር ያለው ሰው ነው። ይህንንም ለማድረግ አባቱን በየቀኑ እየመጡ የሚያስቸግሩትን ሽፍታወች ለመምታት ከጠላቶቹ እጅ መሳሪያ ነጥቆ በማምጣት ሽፍታውን የገደለ ሰው ነው።

3.3.1.13 የጌታነህ አካላዊ አሳሳል

አካላዊ አሳሳል ማለት የገፀባህሪያትን ልዩ ልዩ ምኞቶች፣ ተስፋዎች የመጥላትና የማፍቀር ስሜቶችንና ሰበበ ድርጊቶች በድምሩ በጭንቅላት ውስጥ ተውጠንጥነው ለውጫዊ አለም የሚሆኑትን ስሜታዊነትንና አስተዋይነትን ሁሉ በመቅረፅ የየገፀባህሪያቱ ህሊናዊ መልክ የሚታይበት መንገድ ነው። ጌታነህ ረጅም የሰውነት አቋም፣መካከለኛ የሰውነት ውፍረት ያለው ሲሆን ፀጉሩን የሳደገ ሰው ነው።ጌታነህ ከላይ ቆዳ የሚለብስ እና ከታች ቁመቱ በጉልበታ ተራ የሆነ ሱሪ የሚለብስ ሰው ሲሆን ከላይ ራሱን ይጠመጥማል። እንዲሁም በእጁ የቆዳ መፋቂያ ቢላ የሚይዝ ሲሆን ቢላውን የሚይዝበት ምክንያት ደግሞ የሚሰራውን ስራ አሰንዲገልፅለት ከማሰብ አንፃር ነው።

ገፅ፡-10፡-ገብረሐና፡- እና ማን ይበሉህ? ቆዳ መፋቅ፣ ጀንዲ ማለሰለስ፣ መጠጃ መሸጥ አይደለህም እንዴት ሙያህ?ጌታነህ፡- ነው እሱማ።

ገብረሐና፡- እና ከሰምህ ሌላ በምን ጥሪኝ ነው እምትላት አገሬን?

ጌታነህ፡- እና "ፋቂ ወግድ!፣ ሸማኔ ወዲያ! ቀጥቃጭ ወግድ፣ ድሃ ወዲያ" ተብለንአያዝኑልንም? አይለምኑልንም አለቃ? አገርዎን አያባብሉልንም? ኧረ እባክዎ እባከዎ? እንዲያው በናጠጋው ጊዮርጊስ

3.3.1.14 የጌታነህ ማህበራዊ አሳሳል

ጌታነህ በቆዳ ስራ የተሰማራ እና ድሃ ሰው ሲሆን በማህበረሰቡ ዘንድ በሚሰራው ስራ ምንክንያት የተገለለ ሰው ነው። በስራው ምክንያት ሰዎች እና ማህበረሰቡ በማግለሉ ምክንያት ለሀገሩ መጥፎ አመለካከት ያለው ሰው ነው።ጌታነህ ያላገባ እና በዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ የሚኖር ሰው መሆኑን አጥኚዋ ተውኔቱን ስታነብ ከቃለ ተውኔቶቹ መረዳት ችላለች። የዕለት ህይወቱን የሚያሳድረው ቆዳ በመፋቅ ነው።

ገፅ-12፡-ጌታነህ፡- ፊት ከእፍርታም አገርዎ ጋር ያስታርቁኝ።

ገብረሐና፡- እኔ ሆይ?

ጌታነህ፡- መቼም ከእሰዎ ሌላ የሁሉን ልብ ያማለለ የለ ዘንድሮ።

ገብረሐና፡- እንዴት ጀል?

ጌታነህ፡- ከንጉስ እስከ ገባሪ፣ ከደገኛ እስከ ቆለኛ አንድም በችሎት ችሎታዎ፣ አንድም ባቋቋም ፈጠራዎ፣ ደግሞም በተሸጋሪ ጨዋታዎ ታዋቂ ነዎ። አገር ይሰማዎል።አገር ይታዘዝዎል። ንጉስ ይፈራዎታል። ዝም አይበሉን። እና ... እግዚሃር ቢያሳይዎ፣ መላኩ ቢያመላክትዎ ለምንድን ነው አገርዎ እምትጠየፈኝ አለቃ? ለምንድን ነው እምትገፋኝ? ለምንድን ነው ፋቂ›› እምትለኝ?!

ገብረሐና፡- አገሬ "ፋቂ" ትልሃለች?

ጌታህ በማህበራዊ ኑሮው ከማህበረሰቡ የተገለለ እና በኢኮኖሚ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያለው ሰው ነው። ጌታነህ ያልተማረ ፣ ሚሽት ያላገባ እና በቆዳ ስራው እየተዳደረ ኑሮውን እና ወላጆችን የሚያስተዳድር ነው። ይህንንም ከላይ ካለው ቃለ ተውኔት መረዳት ችለናል ጌታነህ በስራው የተነሳ ማህበረሰቡ እና የሀገር አስተዳዳሪዎች ስላገለሉት አለቃ ገብረ ሃና ቤት ድረስ በመሄድ ህዝቡን እንዲጠዩቁለት የሚለምናቸው ከማህበረሰቡ ጋር ጥሩ ያልሆ ግንኙት እንዳለው የሚያሳይ ነው።

3.3.1.15 የጌታህ ስነ ልቦናዊ አሳሳል

ጌታነህ ህዝቡንና ሀገሩን የሚጠላ በስራው እጅግ የሚሸማቀቅ ሰው ነው። ጌታነህ ከሰው እኩል ሆኖ መታየት የሚወድ ሰው ነው። ጌታነህ አለቃ ገብረሃናን አብዝቶ የሚወድ እና ልክ እንደ ፈጣሪው የሚያያቸው ሰው ነው። ይህም ለአለቃ ገብረሃና የተለዬ ፍቅርና እንክብካቤ አለው።

> *ገፅ-16፡-ጌታነህ፡- አለቃ ይለመኑኝ፤ ይለመኑኝ በናበጋው ጊዮርጊስ? /ጌታነህ እግራቸው ሰር ይወድቃል። አለቃ እግራቸውን ነጥቀው ጭራቸውን አውርደው ሊወጡ ሲሉ፡ ጌታነህ ተስፋ ቆርጦ አንገቱን ይሠብራል። በዚህ ጊዜ ይሁን እየበረረ ይገባል/ ገብረሐና፡- ኧረ ተወኝ።ጌታነህ፡- በናጋባው ጊዮርጊስ?*

ጌታነህ ድሃ ሁኖ መወለድ እጅግ የሚያሳዝነው የበታችነት ስሜት የሚሰማው ሰው ነው። በተለይ ቆዳ መፋቁ ትልቅ መገለልና ከማህበረሰቡ መለየቱ ሀገሩን አብዝቶ እንዲጠላት አድርጓታል። ጌታነህ አንድ ቀን የሀገር መሪ ሆኖ እሱን ያሰቃዩትን ባለ ስልጣኖች እና ህዝብ ጨቁኖ መግዛት የሚፈልግ ሰው ነው።

3.3.1.16 የጌታነህ ሞራላዊ አሳሳል

የጌታነህ ሞራላዊ አሳሳል ሀገሩንና ህዝቡን የማይወድ ሀገሩ ምንም አይነት ችግር ቢገጥማት የማያግዝ። ሀገሩንና ህዝቡ መበቀል የሚወድ ሰው ነው። ይህንንም አጥኚዋ ተውኔቱን በምታነብበት ጊዜ ከቃለ ተውኔቶቹ መረዳት ችላለች።

ገፅ-13፡- ጌታነህ /ደስታ እየወረረው/ በማን እድሌ! ቢሆንልኝማ በማን እድሌ! ... መጀመሪያ ፈረስ እሚያስጋልብ ሳር ቤት አሠራቸዋለሁ። ከዚያ ምድረ ፋቂና እረኛ ሁላ እየነዳሁ፣ሸማኔና ቀጥቃጩን ሁላ እያዳፋሁ፣ ድሃና ገባሪውን ሁላ እያጣፋሁ ወደዚያ ሠፊጎጅ አስገባቸዋለሁ።ገብረሐና፡- ከዚያስ?

ጌታነህ፡- ከዚያማ አንድ ባንድ አፋጥጣቸዋለኋ! /ጥርሱን እየነከሰ/ "አየህ አደል ስድብ ምን ያህል ቁስል እንደሆነ"! እላቸዋለሁ "አየሽ አይደል ... ቆዳ አልፊ መባል ምን ያህል አንደሚያንገበግብ!?" እላቸዋለሁ። አንድ ባንድ!!ገብረሐና- በጄ ...

ጌታነህ፡- ተፍቼባቸው በሩን በዉጭ እዘጋዋለሁ። አክ ብዬ እንትፍ!.. ጥቅጥቅ አድርጌ እደፍነዋለሁ። ከዚያ የባጡን ዙሪያ በእሳት! አያይዘዋለሁ። ከዚያ ጉብታ ላይ ሆኜ እሳቴን እየሞኩ እኖራለሁ። ከዚያ ደሞ

ጌታነህ ብዙውን ጊዜ የበታችነት ስሜት የሚሰማው ሰው ነው።በዚህ የተነሳ ህዝቡን አጥብቆ የሚጠላ ነው።

3.3.1.17 የቦጅሮንድ አሞኜ አካላዊ አሳሳል

አካላዊ የአሳሳል ደረጃ የምንለያቸው ገፀ ባህሪያተበአካላዊ ገፅታቸው ነው። ለምሳሌ ረጅም፣ አጭር፣ ቀይ፣ ጥቁር፣ ወፍራም፣ ቀጭን ... ወዘተ ብለን የምንጠራቸው ማለት ነው። ታድያ ይህ የአሳሳል አይነት ብዙ ጥረትን የማይጠይቅ ለተውኔታችን እንዲመቸን አድርገን የምንስለው የአሳሳል ደረጃ ነው።

ገፅ-20፡- በጅሮንድ አሞኜ ወፍራም እና ረጅም የሰውነት አቋም ያለው ሲሆን ፣ፀይም የሰውነት ቀለም ያለው እና ፀጉሩን ያሳደገ ፣ ሰጉን በአውሬ ቆዳ የጠመጠመ ፣አጭር ቁምጣ ሱሪ የሚለብስ እና ከላይ የነብር ቆዳ የሚለብስ ነው።እንዲሁም ጥይት በእጁ የሚይዝ ነው።

በጅሮንድ፡- /በጅሮንድ አሞኜ ወደ ቤት እየገባ እያለ ጌታነህ "እዚህ ቤት" እያለ ቀስ ብሎ አንገቱን አስገብቶ አየ። ማንም የለም። አመንትቶ አዝግሞ ገባና ከወንበር ተቀመጠ። እሱ ከተቀመጠ በኋላ አንድ ሲያዘከዝክ የደረሰ ፈረስ ሲያንፏርር ተሠማ ወዲያው በሩ በኃይል ተበረገደ፤ ሲያይ አንድ የነብር ቆዳ የደረበ ሰው ከደጃፍ ቆሟል። ለኢልካ ሰባሪነቱ - ባለ ድሪ ሎቲ ጆሮው ላይ አንጠልጥሏል። ፀጉሩን ቅቤ ተቀብቷል። የክንድና ጉልበቱ ነገር ሰማይ ሰበር እሚሉት አይነት ነው -አፈረጣጠሙ። የሃምሳ አራት ዓመት ጎልማሳ ቢኾንም እንደ ወጣት ነው ንቃቱ። በጅሮንድ አሞኘ አባተ ይባላል። አለቃ ገብረሐና እና ተክሌ ከቆጥ እንደተንጠለጠሉ ዓይተውት ይልቁን እርስ በእርስ ተወሻሸቁ። ጌታነህ ፍርሀቱ ከፍርሃት በላይ ኾኖ ተንቀጠቀጠ። ደጋግሞ እጅ ነሳ። ይባስ ብሎ ወደ እርሱ ሲቀርብ የሚገባበት ቸገረው።/

በጅሮንድ፡- አንተ ደግሞ አሸከራቸው መኾንህ ነው?

ጌታነህ፡- የማ - ማን?

ከቃለ ተውኔቱ እንደምንረዳው ጅሮንድ አሞኜ እራሱን ቅቤ የተቀባ እንዲሁም ባለ ድሪ ሎቲ ደጆሮው ላይ ያንጠለጠለ ሲሆን እድሜውም በ50 የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሰው ነው።

3.3.1.18 ቦጅሮንድ አሞኜ ማህበራዊ አሳሳል

በጅሮን አሞኜ ቀማህበረሰቡ ዘንድ የተከለሉ ምንም አይነት የማህበራዊ ግንኙነት የሌለው ሰው ነው። ቦጅሮንድ አሞኜ ከማህበራዊ ኑሮ ስለተገለሉ ጫካ ውስጥ የሚኖር ሰው ነው። ቀድሞ የእቴጌ መነን አጋፋሪ የነበር ... አኹን ሸፍታ እና በጫካ የሚኖር ምንም አይነት ከማህበረሰቡ ጋር ግንኙት የሌለው እና ሰውን እንደ አውሬ የሚያይ ለሰው ልጅ ክብር የማይሰጥ ሰው ነው። በጅሮንድ አሞኜ ያላገባ እና ልጅ የሌለው ሲሆ የሚኖረውም አብዛኛውን ጊዜ በጫካ ውስጥ ነው።

ገፅ-21:-በጅሮንድ፡- አውቀኸኛል ግን?

ጌታነህ፡- ኧረ ... እንዲያውም ... ብቻ የግርማዊ ጃንሆይ ... የአጤ ዮሐንስ ቅርብ ሹም እንደሆኑ እገምታለሁ። እንጂ ... ጌታዬ በጅሮንድ፡ በጅሮንድ አሞኘ አባተ የሚባል ሰመ ብርቱ ሰውሰ አታውቅም?

ጌታነህ፡- ታዋቂ ሸፍታ ...

በጅሮንድ፡- ምን?!

ይህም ቃለ ተውኔት የሚያሳየው በጅሮንድ አሞኜ ሰዎችን በማስፈራት የሚያምን እና ከሰው ልጆች ጋር ጥሩ የሆነ ግኝኑት የሌለው ሰው ነው። በጅሮንድ አሞኜ በየቀኑ ሰዎችን የሚያሳድድ በማህበረሰቡ ዘንድ የተጠላ እና የተገለለ ሰው ነው።

3.3.1.19 ቦጅሮንድ አሞኜ ስነ ልቦናዊ አሳሳል

የገፀባህሪያትን ልዩ ልዩ ምኞቶች፣ ተስፋዎች የመጥላትና የማፍቀር ስሜቶችንና ሰበበ ድርጊቶች በድምሩ በጭንቅላት ውስጥ ተውጠንጥነው ለውጫዊ አለም የሚሆኑትን ስሜታዊነትንና አስተዋይነትን ሁሉ በመቅረፅ የየገፀባህሪያቱ ህሊናዊ መልክ የሚታይበት መንገድ ነው። የበጅሮንድ አሞኜ ስነልቦናዊ አሳሳል ስንመለከት በጅሮንጅ አሞኜ

ገፅ-21:-በጅሮንድ:- አይ እንግዲህ! ... ምንድን ነው ዐመሌን የማያዉቁ መምሰል እዚህ!? ... ቢያምርብዎ አንዲት ዘገር ሳትነቀነቅብዎ ያልኩትን ይፈፅሙ፣ ያለዚያ ግን ንፍር ዉሃ ቀቅሎዎ ነዋ ያውም እሚራዱን። /ወደ መድረኩ የቀኝ ታችኛ ተገነጠለ - ለጎንታ/ እናንተ ዝነኞች አግዙን እንጂ ያዳግተናል ብቻችንስ።... መቼም ሀገር እምታዉቀውን ሰው ማቀፍ ከሀገር የመተቃቀፍ ያህል ነው። ... ወደው ነው "አሁንማወደሸ ነው ገጣቢት ንጉሰ ምትመርቂ!!?

ገብረሐና:- /ለበጣ/ አስቆጣሁህ መሠል።

በጅሮንድ: ይመስለኛል ... ብቻ እንጃ ያለፈው አልፏል ከዚህ በኋላ ባያስቆጡኝ ነው የሚሻለው... /በሚያሳጣ ለበጣ

በጅሮን አሞኜ አትጌ መነን አጥብቆ የሚወድ ለስልጣን ሹኩቻ የሚገጥም ሰው ነው። በጅሮንድ የሰው ልጆችን ከሚሰጣቻው ሰዋዊነታዊ ክብር በታች አሳንሶ ማየት የሚያስደስተው ሲሆን አስተዋይነት የሌለው ሁሉን ነገር በሀይል ማድረግ የሚያስደስተው ነው።

3.3.1.20 ቦጅሮንድ አሞኜ ሞራላዊ አሳሳል

ተፈጥሮ ከሚፈቅደው በታች ወርዶ ቅጥ ያጣ ስግብግብ ሆኖ ሲቀርብ ወይም ከሚገባው በላይ ክብር ፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም ከሁለቱ በተቃራኒ አለማዊና መንፈሳዊ መመሪያዎችና ህጎችን ተቀብሎ የሞራል አስተማሪና ሰባኪ ሲሆን በሚያሳዩና በመሳሰሉት ፍሬ ሀሳቦች ላይ በማተኮር ገፀባህሪያቶችን ከዚህ አንፃር በመቅረፅ ላይ ያነጣጥራል።

በጅሮንድ አሞኜ እድግ ሲበዛ ጨካኝና አረመኔ ሰው ነው።በተለይ ሀገር አስተዳድራለሁ በማለት አለቃ ገብረሃና እንዲከተሉት ቤታቸው ድረስ በመሄድ የሚያስፈራራ ሰው ነው። እንዲሁም እራሱን ከሌሎች ከፍ አድርጎ የሚያይ ሰው ነው።

ገፅ-21:-በጅሮንድ:- አውቀኸኛል ግን?ጌታነህ:- ኧረ ... እንዲያውም ... ብቻ የግርማዊ ጃንሆይ ... የአጤ ዮሐንስ ቅርብ ሹም እንደሆኑ እገምታለሁ። እንጂ ... ጌታዬ ...በጅሮንድ: በጅሮንድ አሞኘ አባተ የሚባል ሰመ ብርቱ ሰውሰ አታውቅም?

አጥኚዋ ቃለ ተውኔቱን በማንበብ የቦጅሮን አሞኜን ሞራላዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል መረዳት ችላለች። በጅሮንድ አሞኜ ከሚባለው በላይ ሰዎች ክብር እንዲሰጡት የሚፈልግ እራሱን ከሌሎች ሰዎች በላይ ነኝ ብሎ የሚያስብ እና ለራሱ ክብር የሌለው ፍጡር ነው። በጅሮንድ አሞኜ ለህጎችና ደንቦች የማይገዛ ሁሉን በኃይ ለማከናወን የሚወድ ነው። የበጅሮንድ አሞኜን ምሞራላዋዊ አሳሳል አነጥኚዋ በተለይ ቴአትሩን በማየት በሚያደርጋቸው የሰውነት

እንቅስቃሴዎች እና ድርጊቶች በመነሳት ለመሳል ችላለች።

3.3.1.21 የወታደር አካላዊ አሳሳል

ወታደር አንድ እግሩ የሚያነክስ ወፍራም የሰውነት ቅርፅ ያለውና እና መካከለኛ የሰውነት ቅርፅ ያለው ሰው ሲሆ ጥቁር መልክ ሲኖረው እራሱ ላይ በአውሬ ፀጉር የተሰራ ቆብ ያደረገ ሰው ነው። ወታደር በእጁ ጠበንጃ የያዘ ሲሆን ከላይ ጃኬት ከታች አጭር ሱሪ የለበሰ ነው።

> *ገፅ-49:- ወታደር:- (ይቆጣል) አሁን ለዋዛ ፈዛዛ አይደለም የመጣሁት። በጅሮንድ አሞኜ አለቃዬ ጠበቅ፣ መረር ያለ ትዕዛዝ ሰጥቶኝ ነው የመጣሁት።*
>
> *ገብረሐና:- ምን ይሆን ጠበቅ፣ መረር ያለው ትዕዛዝ?*
>
> *ወታደር:-የተሰጦ የሳምንት እድሜ አልቋል። የተባሉትን ነገር ፈፅመው ከሆነ እሰይ ... ካልሆነ ግን ...*
>
> *ገብረሐና:-ካልሆነ ግን?*
>
> *ወታደር:-አበሳዎን አሳይቼ ልገላግልዎ ነዋ አመጣጤ! (ጎራዴውን ይመዛል)*

ወታደር ቀስ ብሎ የማይነገር እና በእጁ ጥይት የያዘ ሲሆን ፀጉሩንና ፂሙን ያሳደገ እና ወጣት ነው።

3.3.1.22 የወታደር ማህበራዊ አሳሳል

ወታደር ከማህበረሰቡ በመገለላቸው ምክንያት ከነ በጅሮንድ አባተ ጋር በሽታነት ህይወት የሚኖር የሀገሩን ህዝብ በጭቆና ማስተዳደር የሚፈል። የቦጅሮንድ አገልጋይና ጠባቂ ሲሆን ለቦጅሮንድ መልዕከትና ተልዕኮ በማስፈፀም ህይወቱን የሚመራ ሰው ነው።

> *ገፅ-55:-ወታደር:-የተባልከውን አትናገርም አንተ እንከፍ (ጎራዴውን መዝዞ የጌታነህን አንገት ሊቀላ ሲዘጋጅ ድንገት ተኩሰ ይሰማና ተከታትሎ ነጋሪት ይጎሰማል፤ ፉከራና እልልታ ሸለላ ይድብለቀለቃል የመድፉና የጠመንጃው ተኩሰ ያይላል። ማዘንጊያሸ እንሰራዋን አዝላ "እልል" እያለች ትገባለች። የማዘንጊያሸን እልልታ ተከትሎ አዋጁ ጎልቶ ይሰማል።)*

ወታደር ያላገባ በሽፍትነት ህዎት የሚተዳደር ከሰዎች ጋር ጥሩ ያልሆነ ግንኙት ያለው በሰዎች ዘንድ የተጠላ ሲሆን በውትድርና ህይወት እራሱን ያሰማራ ሰው ነው።ወታደር የስራ ሀላፊነቱ ለበጅሮንድ መላላክ ሲሆን በተለይም ሁሉን ነገር ለመስፈፀም በሀይል የሚያደርግ ነው።

3.3.1.23 የወታደር ስነ ልቦናዊ አሳሳል

የገፀባህሪያትን ልዩ ልዩ ምኞቶች፣ ተስፋዎች የመጥላትና የማፍቀር ስሜቶችንና ሰበበ ድርጊቶች በድምሩ በጭንቅላት ውስጥ ተውጠንጥነው ለውጫዊ አለም የሚሆኑትን ስሜታዊነትንና አስተዋይነትን ሁሉ በመቅረፅ የየገፀባህሪያቱ ህሊናዊ መልክ የሚታይበት መንገድ ነው።

ወታደር እጅግ ሲበዛ ሰውን መጨቆን የሚወድ ርህራሔ ሚባል የሌለው እና ስልጣን የሚወድ ሰው ነው። ወታደር ለሰው ልጆች ክብር መስጠት የሚያሳፍረው ሰው ነው።

> *ገፅ-41:-ወታደር:- ዐጤ ዮሐንስ እኮ ሞቱ! ደስ አይልም? ደ - ስ እንዳለን ደስ ይበልዎ'ጂ አለቃ። ... ጌታዬ በጅሮንድ አሞኜ አባተ፤ ለፈረሳቸው ሰም አውጥተው፣ ሰምንት ሺ ወታደራቸውን አንጋግተው ድፍን ኢትዮጵያን ሊያስገብሩ መንገድ ገብተዋል።/ይልቁን በደስታ እጅ እየነሳቸው/ ... ለእስካሁን እገዛዎ እጅ እንሳለን። እስዎ ከዘመቻው ባይቀሩ ኖሮ፣ እስዎ ሰለዐጤ ዮሐንስ ደካማ ጎን ባያስመለክቱን ኖሮ፣እስዎ የምኒልክን ጥልቅ ምኞት ባያስገነዝቡን ኑሮ፤ ጌታዬ በጅሮንድ አሞኜ - የሠው ወንጭፍ - እንዲህ ተሥፋቸው ባልቀና ነበር። ገና ገና ... ካሁን አሁንየእስዎን መለ እየተጠባበቁ ነው ጌታዬ። የኢትዮጵያ አልጋ እኮ ባዶ ሆነ አለቃ!በደስታ አያሸበሸቡም?ገብረሐና:-/ማሸላ ሲያር የሚሰቀውን ሳቅ ሳቁ በረዥሙ።/ ይኸው ነው በቃ?ወታደር:- በቃ*

በመሆኑም አጥኚዋ የወታደርን ስነ ልቦናዊ አሳሳል ተውኔቱን በማንበብ መረዳት እና መተንተን ችላለች። ወታደር ስልጣንን አብዝቶ የሚናፍቅ እና ያለ መመሪያ እና ደንብ በሀይል ሰዎችን መግዛት የሚወድ ሰው ነው። ወታደር ለሰው ልጅ ክብር መስጠት የሚያሳፍረው እና ሸንፈት መስሎ የሚታየው ሰው ኘው።አጥኚዋ የወታደርን ስነ ልቦናዊ አሳሳል ስትስል ከቃለ ተውኔቱ በተጨማሪ ቴአትሩን በመመልከቶ ከሚያደርጋቸው ድርጊቶች እና እንቅስቃሴዎች በመነሳት ለመሳል ችላለች።

3.3.1.24 የወታደር ሞራላዊ አሳሳል

ወታደር በሰው ላይ ክፉ ነገር መስራት የሚያስደስተው ፣ ለሀገሩና ለህዝቡ የማያዝን ጨቃኝ ሰው ነው። እንዲሁም እራሱን ከሌሎች ከፍ አድርጎ የሚያይ እና ከእኛ በላይ ሰው የለም በማለት የሚያስብ ሰው ነው።

> *ገፅ-50:-ወታደር:-ስንት ቅኔ የሚፈቱት ታላቁ ሰው ይኼ የተራ ሰው ንግግር አልገባ አልዎ! (ይስቃል) እንግዲያውስ ይረፉት (ገመድ ያወጣል) በጅሮንድ የላኩኝ መልዕክተኛው የሚያመጣውን መልስ ለእኛ ንግሥና የሚጠቅም ከኾነ አለቃን በሰላም ትተሃቸውና ለውለታቸውም ሹመትና ሽልማት እንሰጣቸዋለን። የመጣው መልስ ለእኛ መጥፎ ከኾነ ግን ዛሬውኑ እስከ መላው ቤተሰባቸው ገድለሃቸው በጎጇቸው ላይ እሳት ልቀቅበት እና ና*

ብለው ነው የላኩኝ። (ይስቃል) አሁንስ ገባዎት?ገብረሐና፡-መግደሉንስ ግደለኝ ... እሳት ምትለቅብን ምን ብትከፋ ነው ልጄ?ወታደር፡-አይዞ አይስጉ ከሞቱ በኋላ እሳት ቢለቀቅብዎ በድኖ አይለማ አይሰማ!!ገብረሐና፡-አሃ እንደዛ ነው እንዴ፣? ... እኔ ደግሞ ከሞትኩ በኋላ የሚሰማኝ

ወታደር ሰዎችን የማያከረብ እና ሰዎች እንዲያከብሩት የሚፈልግ ሲሆን እንዲሁም ሰዎችን ያለ ህግና ደንቡ መብታቸውን በመጣስ ማስተዳደር የሚፈልግ ሲሆነ ከሚገባው በላይ ክብር ፈላጊ ነው።

3.4 የሴራ

"የሸምጋይ" ተውኔት ከሴራ አይነቶች መካከል በአንዱ የሚካተት ሲሆን ጥምር የሴራ አይነት ያለው ነው። ይህም ጥምር የሴራ አይነት የያዘ ሲሆን የመጀመሪያ ሴራ አለቃ ገብረሃና ከሚስታቸው ጋር የሚያደርጉት ጭቅጭቅ እና ንትርክ የሚያመለክት ሲሆን አለቃ ገብረሃና ሚስታቸው ምግብ አሳንሳ ስታቀርብላቸው አልበላም ብለው በመቆጣታቸው ሚስታቸው ማዘንጊያሽም እንዲበሉ ሳትለምናቸው ምግቡን ወስዳ በማስቀመጧ እግጅ ተናደው ለጦርነት ወደ ንጉስ ዮሐንስ ለመሄድ እንደተዘጋጁ እና ፈረሳቸውን እንድታዘጋችላቸው ሲያዙዟት ወዲያው ማዘንጊያሽም ፈረሶችን ለማዘጋጀት ወደ ውጭ ስትሄድ ከጓዳ ገብተው ምግብ ሲሰርቁ ስደርስባቸው አፍረው ይወጣሉ። ይህንንም አለቃ ገብረ ሃና ያደረገበት ምክንያት ሚስታቸው ሌለላ ወንዶች ታበላለች በማለት ለመበቀል በማሰብ ነው ። ሌላኛው ሴራ ደግሞ ጌታነህ አለቃ ገብረሃናን ከህዝቡ ጋር እንዲያስታርቁት የሚለምናቸው ነው ይህም ጌታነህ በሚሰራው የቆዳ ስራ ምክንያት ከህዝቡ መገለሉ የበተችነት ስሜት እንደተሰማው እና አለቃ ህዝቡን እንዲነግሩለት እና እንዲያስታርቁት ከእግራቸው ተደፍተው ሲለምናቸው አለቃም እሂነን ቢናገሩ ማንም እንደማይሰማቸው እና በሚሰራው ስራ ስሙን ተቀይሮ ቢጠራ የሚያሳፍር ነገር እንዳልሆነ ይነግሩታል። እንዲሁም አለቃ ገብረ ሃና ልጃቸው ተክሌንና ልጃቸው ጥሩነሽን የቅስና ትምህርት በሚያስተምሩበት ወቅት በማህበረ ቅዱሳን ህግ ና ደንብ ውስጥ የማይፈቀድ የቅኔ አቀፃፀል ዘዴ ሲያስተምሯቸው ተክሌ ግን እንደተከለከለ እና የቤተክርስቲያኑን ህግ ማክበር እንዳለባቸው ለአለቃ ሲነግራቸው አለቃ ምንም ነገር ማምጣት እንደማይችሉ እና እንዲቀፅሉት ለልጃቸው ይነግሩታል። ሌላኛው የሴራ አይነት ደግሞ አለቃ ገብረሀና ኗጅሮንድ አሞኘ እያስፈራራቸው እና እየዛተባቸው የሚያሳይ ነው።ይህም በጅሮንድ አሞኘ አፄ ሚኒሊክንና አፄ ዮሐንስን ከመደገፍ አቁመው እነሱን እንዲከተሉና የእትጌ መነን ስልጣን እንዲመለስ መስራት እንዳለባቸው ለአለቃ ገብረሃና እያስፈራራ ቢነግሯቸውም አለቃ ግን እሂንን ማድረግ እንደማይችሉ ደጋግመው በምሳሌ እና በቅኔ ቢነግሩትም አልገው ሲል አስጠንቅቋቸው ወጥቶ ይሄዳል። ወዲያውንም በጅሮን አሞኜ ወታደሩን ልኮ በድጋሜ ሀሳባቸውን ቀይረው እንደሆነ ቢያስጠይቃቸውም ለወታደሩ ሀሳባቸውን እንደማይቀይሩ ይነግሩታል። በዚህ ጊዜ ወታደሩም ማስፈራሪያ በተላበሰ ዛቻ ቢያስፈራራቸውም እንደማቀይሩ ደጋግመው ሲነግሩ በጣም ተናዶ ጥይቱን ግንባራቸው ላይ እንደደቀነባቸው ከውጭ ባለ ጥይት ተመትቶ ይወድቃል። ሌላኛው ሴራ ደግሞ ጌታነህ ከአለቃ ገብረሃና ቤት

መሄድ ማህበረሰቡንና ንጉሶችን ቆዳ መፋቅ የተከበረ ስራ እንደሆነ እና ከሰው እኩል እንደሆኑ ከዚህ በኋላ ከሌሎች ሰዎች ተለይተው መታየት እንደሌለባቸው እንዲነግሩለት ከጉልበታቸው ወድቆ ሲለምናቸው አለቃ ገብረሃናም ህዝቡ እሳቸውን እንደማይሰማቸው እና ከሰማቸውም መይሰው ካሳን ይሰማቸው ነበር ብለው ተስፋ አስቆርጠው ወደ ቤቱ እንዲሄድ ካደረጉት በኋላ ሁለቱን ልጃቸውን የቅፀላ ትምህርት እያሰጠኗቸው እያለ ወታደር በድጋሜ ወደ ቤታቸው ይገባ እና አለቃ ገብረሃናን ጉዳይ የሚያስፈፅሙትዐቀን እንዳለቀ እና የተሰጣቸው ትዕዛዝ ምን ላይ እንዳደረሱት በማስፈራራት ሲጠይቃቸው አለቃም ምንም አይነት ትዕዛዝ መቀበልና ማስፈፀም እንደማይፈልጉ በቅኔ ሲነግሩት ወታደሩም አለቃ ገብረ ሃና ትክሻ ላይ ጥይት ይደቅንባቸዋል ከዛም አዋጅ ይነገራል።አለቃ ገብረሃናም አዋጁን እንደሰሙ አፄ ሚኒሊክ የኢትዮጵያ መንግስት ሁነው መሾማቸውን ሲሰሙ በደስታ ጮቤ ይረግጣሉ ወታደሩነም አሂንን በሰማ ጊዜ አለቃን እስከነ ቤተሰባቸው ለመግደል በወሰነበት ቅፅበት ከሩቅዐበተተኮሰ ጥይት ተመትቶ ይወድቃል ተክሌም መሞቱን ሲያውቅ ጥይቱን ትክሻው ላይ አድርጎ በኩራት ይገባል። ከዛም ኢትዮጵያ ወደ አንድ ትልቅ ግዛት ትመጣለች።

3.5 ቃለ ተውኔት

ቃለ ተውኔት ገፀባህሪያቶቹን ከስማቸው ጀምሮ እነማን እንደሆኑ የስራ፣ የኑሮ የመሳሰሉትን ሁኔታዎች ያሳውቀናል። የየገፀባሀሪያቶችን ባህሪ ያሳየናል የአሳሳል ደረጃቸውን ያሳውቀናል። የታሪኩ አንዱ አካል የሆኑ ነገር ግን መድረክ ላይ ሊፈፀሙ የማይችሉ ከመድረክ ጀርባ የተከናወኑ ድርጊቶችን በቃለ ተውኔት ምክንያት ምን እንደሆኑ ምን እንደነበሩ ለማወቅ እንችላለን። ከቃለ ተውኔት ጠቀሜታዎች እንደምንረዳው የተውኔቱ ግማሽ አካል በቃለ ተውኔቱ እንደተደገፈ ነው። ቃለ ተውኔት ሲፃፍ ተውኔቱ የሚቀርብላቸውን ሰዎች በደንብ ማወቅ ተገቢ ነው ይህ ካልሆነ ግን በቃለ ተውኔት ማስተላለፍ የተፈለገው መልእክት መና ሆኖ ይቀራል ማለት ነው። ቃለ ተውኔት፣ግልፅ ተገቢ፣ትክክለኛ፣እውነተኛ መሆን መቻል አለበት። በመሆኑም አጥኚዋ በሸምጋይ ተውኔት ውስጥ ያሉ ቃለ ተውኔቶች አንዳንድ ቦታ ላይ ግልፅ ያልሆኑና አሻሚ የሆኑ ቃለ ተውኔቶችን መመልከት ችላለች። ለምሳሌ ያህል:- ጥሩነሽ እና ተክሌ በሚያወሩበት ስዓት ግልፅ ያልሆነ ቃለ ተውኔት ብዙውን ስዓት ይጠቀማሉ።እንዲሁም ማዘንጊያሸና አለቃ ገብረሃና በሚጨቃጨቁበት ስዓት የጭቅጭቁ መንስኤ በግልፅ ቢታዎቁም በምን ስዓት እንደተታሩቅ ግልፅ አድርጎ የሚያስረዳ ቃለ ተውኔት አይጠቀሙም። በመሆኑም የሚጠቀሟቸው ቃለ ተውኔቶች አንዳንድ ቦታ ላይ ግልፅ አለመሆናቸው አጥኚዋ ግልፅ ያልሆነና ተገቢ ያልሆነ ቃለ ተውኔት እንዳለ መመልከት ችላለች። ለምሳሌ ከነዚም ቃላቶች ውስጥ ቆለምሻሽ ፣ ሰገባ ፣ ኩሮ ፣ ይሳነት ፣ ኢልካ የሚሉ ቃለ ተውኔቶች አጥኚዋ ተውኔቱን በምታነብበት ስዓት በቀላሉ ልትረዳቸው ማለመቻሏ የተለያዩ ሰዎችን በመጠየቅ እና የአማርኛ መዝበ ቃላት በመጠቀም ትርጉማቸውን ለመረዳት ችላለች።

3.6 ጭብጥ

ጭብጥ ማለት በምዕራፍ ሁለት እንደተመለከትነው ከተውኔት አላባዊያን ውስጥ አንዱ ሲሆን ጭብጥ በዋናነት

በታሪኩ ውስጥ እንዲተላለፍ የተፈለገው ዋና ሃሳብ ወይም መልዕክት ነው። "የሸምጋይ" ተውኔት የሚያስተላልፈው ዋና መልክት በቀደሙት የኢትዮጵያ የመንግስት ስርአት አምባገነነኝ የነበረበትና ተከፋፍላ በንጉሳዊ የመንግስት አገዛዝ አማካኝነት ትመራ እንደነበር እንዲሁም የቆዳና የሸመና ስራን መስራት በማህበረሰቡ ዘንድ እጅግ አፀያፊ እንደነበር እሂን ስራን ሚሰሩ ሰዎች እንደሚገለሉ የተውኔቱ ዋና ሃሳብ ይገልፃል። በተጨማሪም አለቃ ገብረሃና በዛን ዘመን የነበሩ ትልቅና የተከበሩ አባት እንደነበሩ እንዲሁም ችግሮችን በቅኔ መፍታት የሚያስደስታቸው ሰው መሆናቸውን ጭብጡ ይናገራል።

ምዕራፍ አራት

4. ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳብ

4.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የኢትዮጵያ የቀደሙት የመንግስት ስርዓቶች ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ሲሆን በተለይ በቀደምት ዘመናት የነበሩትን የኢትዮጵያ ነገስታት ንግስናን ስርዓት በሀይል ማግኘት እንደሚችሉ የሚያሳይ ሲሆን ኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ ነገስታት እንደነበሩ ይገልፃል። እንዲሁም በዛን ዘመን እጅግ ታዋቂ እና በቅስና ትምህርታቸው ላይ ሊቅ በሆኑት በአለቃ ገብረሃና አሸሙር እና ምሳሌያዊ አነጋገር ላይ የሚናገር ሲሆን ሀገራችን ኢትዮጵያ በቆዳ እና በሸመና ስራ ላይ ተሰማርቶ መስራት ከማህበረሰቡ እንደሚያስገልል ጭምር ይገልፃል። ይሁን እንጂ አጥኚዋ ቴአትሩን ከተውኔት አላባዊያን አንፃር በምትሰራበት ወቅት ያገጠሟትን ችግሮች ለወደፊት ቢስተካከል አሪፍ ነው በማለት ዘርዝራ አስቀምጣቸዋለች።በመሆኑም ተውኔቱ ሲፃፍ ለአንባቢያን አስቸጋሪ፣ አሻሚ እና ግልፅ ያልሆኑ ቃለ ተውኔቶች መኖራቸው በደንብ ለመረዳት አሰቸጋሪ እንደሆነ አጥኚዋ ተመልክታለች። እንዲሁም የመቼት ቦታው አለመቀያዩሩ እና አንድ የቦታ መቼት ላይ መሰራት መቻሉ ተመልካችንጓጉቶ ሌላኛውን ትዕይንት እንዳይመለከተው ሊያደርግ ይችላል በማለት ቴአትሩን ቴአትሩን በመመልከት እንደ ውስንነት ለማስቀመጥ ችላለች። በመሆኑ ሸምጋይ ቴአትርን ለሚያዘጋጁ አጥኚዎች እና ተውኔት ለሚፅፉ ባለሙያዎች እነዚህን ክፍተቶች አስተካክለው ቢሰሩ ቴአትሩ የተሟላ እና ግልፅ መልእክት ይኖረዋል የሚል ሐሳብ አጥኚዋ አስቀምጣለች።

4.2 የመፍትሔ ሃሳብ

ከዚህ በኋላ ተውኔት መፅሀፍም ሆነ ቴአትር ማዘጋጀት ለሚፈልጉ ሙያተኞችም አጥኚው " በሸምጋ " ተውኔት ላይ ያየቻቸውን ክፍተቶች አሟልተው ቢያዘጋጁ ማለትም አሻሚ የሆኑ ቃላቶች ባይኖሩ እና መደበኛ የሆኑ ቃለ ተውኔቶችን ቢጠቀሙ ጥሩ ነው ብላ አጥኚዋ እንደ መፍትሔ አስቀምጠዋለች።አንዲሁም አጥኚዋ ጥናቷን በምሰራበት ወቅት ያጋጠማትን የቴአትሩን አዘጋጅ ስለ ተውኔቱ ምንነት የቃለ ቃለ ተውኔ ሁኔታ ቃለ መጠይቅ በማድረግ እንዲሁም አንዳንድ ቃላቶችን መዝገበ ቃላት በመጠቀም የገጠማትን ችግሮች ለመቅረፍ ሞክራለች።

ጥቅሶች ከመገኛ ቋንቋቸው

1. The history of theater dates back to ancient civilizations, with evidence of theatrical performances found in cultures such as ancient Greece, Rome, Egypt, and China. In ancient Greece, theater was an integral part of religious festivals, and plays were performed in outdoor amphitheaters. The works of playwrights like Aeschylus, Sophocles, and Euripides are still celebrated for their enduring impact on theater.During the medieval period, theater evolved into religious plays performed in churches, and later, secular plays performed by traveling troupes. The Renaissance brought about a resurgence of interest in classical Greek and Roman theater, leading to the establishment of permanent theaters and the professionalization of acting companies.In the 17th and 18th centuries, European theater experienced significant developments, with the emergence of influential playwrights such as Molière, Shakespeare, and Ibsen. The 19th century saw the rise of realism in theater, as well as the development of new theatrical forms such as melodrama and musical theater.In the 20th century, theater underwent radical changes with the advent of avant-garde movements, experimental theater, and the influence of groundbreaking playwrights and directors such as Bertolt Brecht, Antonin Artaud, and Constantin Stanislavski. This period also saw the rise of modernist and postmodernist approaches to theater, as well as the development of new forms of performance art and multimedia theater.Today, theater continues to evolve with the incorporation of new technologies, diverse storytelling techniques, and innovative approaches to staging and performance. It remains and engages with the social, political, and cultural issues of our time.

ዋቢ መፅሀፍት

የሻው ተሰማ ። የተውኔት አፅናፍ መነፅር ። አዲስ አበባ ፣ ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ድርጅት ፣ 1998።

ያለው እንዳወቅ። (2006) ። የምርምር መሠረታውያን እና አተገባበር ። አዲስ አበባ ፣
ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

አለም እሸቱ።(1995)። መሠረታዊ የምርምር ሚና የዘገባ አዛዛፍ አፃፃፍ ዘዴ። አዲስ አበባ፣
ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ዘሪሁን አስፋው ። የስነፅሁፍ መሰረታዊያን ። አዲስ አበባ ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት ፣ 1992 ።

ደበበ ሠይፉ። (1973) ። የቴአትር ጥበብ ከጸሐፌ -ተውኔቱ አንፃር። አዲስ አበባ፣ ንግድ
ማተሚያ ቤት።

ፋንታሁን እንግዳ ። ተውኔታዊ መዝገባ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ከ ሀ እስከ ፐ። አዲስ አበባ፣ ብርሃን እና
ሠላም ማተሚያ ድርጅት ፣1993።

_____ የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ። አዲስ አበባ ፣ ብርሃን እና ሠላም ማተሚያ ድርጅት
፣ 2005።

_____ የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ። አዲስ አበባ ፣ ብርሃን እና ሠላም ማተሚያ ድርጅት ፣ 1992።

ሔለን ልዑል ። ኦዲፐስ ንጉር ታሪካዊ ተውኔት ከተውኔት አላባዊያን አንፃር። አዲግራት ፣ ያልታተመ ፣ ለቴአትር
አርትስ ባችለር ድግሪ ማሟያ የተዘጋጀ ጥናታዊ ፅሁፍ ፣ 2013።

ROBERT SWAIN . DIRECTING A HANDBOOK FOR EMERGING THEATRE DIRECTORS.
UNITED KINGDOM , 2011

አባሪ

አባሪ 1

ሸምጋይ ፅሁፈ ተውኔት